የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.22
ADDIS ABABA 24th January, 2018

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፳፫/፳፻፲ ዓ.ም

የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..........................................ገጽ ፲ሺ፺፩

## Content

Regulation No. 423/2018

Mining Operations Council of Ministers Regulation ........................... --Page 10,091

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፫/፳፻፲

## ስለማዕድን ሥራዎች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፳፻፯ አንቀጽ ፭ እና በማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፳፻፪ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፲፮/፳፻፭ እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፹፪ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፫/፳፻፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር፦

፩/ በማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፳፻፪ (እንደተሻሻለ) የተሰጠ ትርጉም ተፈጻሚ ይሆናል፤

## Council of Ministers Regulation No.423/2018

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR MINING OPERATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 Article 5 and Article 82 (1) of Mining Operations Proclamation No. 678/2010 (as amended by Proclamation No. 816 /2013)

### PART ONE

### GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Mining Operations Council of Ministers Regulation No. 423/2018".

**2. Definitions**

In this Regulation unless the context requires otherwise:

1/ the definitions provided in the Mining Operation Proclamation No.678/2010 (as amended) shall apply;

ያንዱ ዋጋ Unit Price 42·60

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ "ስምምነት" ማለት የማዕድናት ቅኝት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየትና የማምረት ሥራዎችን ለማካሄድ በመንግሥትና በባለፈቃድ መካከል የሚደረግ ውል ነው፤

፫/ "የማህበረሰብ ልማት" ማለት የማዕድን ሥራ በሚካሄድበት የፈቃድ አካባቢ የሚገኘውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚከናወን የማህበራዊ፣ ኢኮሚያዊ እና የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ነው፤

፬/ "ማማከር" ማለት በማዕድን ዘርፍ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የሚሰጠው አገልግሎት ነው፤

፭/ "የልማት ፕሮግራም" ማለት ማዕድን ማምረት ከመጀመሩ በፊት የሚከናወን የመሠረተ ልማት አውታር ግንባታ፣ የመሬት ገጽታ ለምርት ሥራ ዝግጁ የማድረግ ሥራ፣ የምድር ውስጥ ለውስጥ መግቢያ ቁፋሮ ሥራ፣ የማዕድን ማምረቻ መሣሪያዎች ግዥ፣ ማጓጓዝና ተከላ፣ የምርት ሙከራ እና የመሳሰሉ ሥራዎችን የሚያካትት ነው፤

፮/ "ግኝት" ማለት ከዚህ በፊት ብቸኛ የሆነ መብት የሚያሰጥ የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ባልተሰጠበት ወይም ማመልከቻ ባልቀረበበት ወይም ባልተከለከለበት እና ማዕድን መኖሩ ከዚህ በፊት ባልታወቀበት ቦታ ላይ በተፈጥሮ መልኩ መኖሩን ወይም የማዕድኑ መኖርን የሚያሳይ ምልክት ማግኘት ነው፤

፯/ "የገንዘብ አቅም" ማለት የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የጠየቀ ማንኛውም ሰው ቢያንስ ለመጀመሪያው ዓመት ያቀደውን የማዕድን ሥራ ለማከናወን በሀገር ውስጥ ባንክ ያስቀመጠውን ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ መጠን የሚያሳይ ማረጋገጫ ሰነድ ነው፤

፰/ "የፋይናንስ ሁኔታ" ማለት እንደነገሩ ሁኔታ የገንዘብ አቅምን ጨምሮ አመልካቹ ላቀደው የማዕድን ሥራ ሊያውለው ያዘጋጀውን የገንዘብ መጠን የሚያሳይ ማስረጃ ነው፤

፱/ "ፈንድ" ማለት አግባብ ባላቸው ሕጎች እና በስምምነት በሚወሰነው መሠረት የማዕድን ሥራ በሚከናወንበት ቦታ እና በፈቃድ ክልል አካባቢ ለሚደርሰው የአካባቢ ተፅዕኖ መልሶ ማቋቋሚያና በማህበረሰብ ልማት ዕቅድ ለመሳተፍ በባለፍቃዱ የሚመደብ ገንዘብ ነው፤

2/ "agreement" means a contract concluded between the Government and the licensee in order to conduct reconnaissance, exploration, retention and mining;

3/ "community development" means economic, social and environmental protection activity under taken around the license area to benefit the local community;

4/ "consultancy" means a service rendered by a professional having certificate of professional competence in the mining sector;

5/ "development program" includes pre-production works involving erection of infrastructure, making the surface of the earth ready for mining, excavation of underground entrance, and procurement, transportation and plantation of mining equipments, production test, and of other similar activities;

6/ "discovery" means an identification of the existence or an indication of minerals where the minerals were not previously discovered in the area in question and are not subject to exclusive right or an application thereof or have not been reserved;

7/ "financial position" means a document submitted by an applicant which verifies the proportional amount of money deposited at domestic bank to guarantee the execution of the proposed work plan at least for the first one year;

8/ "financial situation" means evidence that reveals the applicant's amount of money prepared for his mining operations plan including his financial position, as the case may be;

9/ "fund" means the amount of money allocated by the licensee pursuant to the appropriate laws and agreement in order to rehabilitate the license area and the area surrounding the license area to participate in community development plan;

፲/ “የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ” ማለት የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ማንኛውም ሰው ማመልከቻውን ለማስመዝገብ የሚከፍለው የመመዝገቢያ ክፍያ ነው፤

፲፩/ “ብሎክ” ማለት አጠቃላይ የፈቃድ ክልሉን በማከፋፈል በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ መሠረት የሚገኝ አንድ ድርሻ ነው፤

፲፪/“የአፈጻጸም ሪፖርት” ማለት የማዕድን ሥራ ባለፈቃድ በገባው የፈቃድ ስምምነት መሠረት ያከናወናቸውን ዝርዝር ተግባራት እና ያገኛቸውን ውጤቶች እንዲይዝ አድርጎ የሚያዘጋጀው የቴክኒክ እና የፋይናንስ አፈጻጸም ዘገባ ነው፤

፲፫/“አዋጅ” ማለት የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፪ሺ፪ (እንደተሻሻለ) ነው፤

፲፬/“የማዕድን ናሙና” ማለት ለንግድ ባልሆነ መጠን ከተፈጥሮ ስፍራው የተወሰደ ለጥናትና ምርምር፣ ለላቦራቶሪ ምርመራ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ፕሮሰስ ተደርጐ ለገበያ ለማስተዋወቅ ወይም አግባብ ላለው ሌላ ዓላማ የተዘጋጀ ማዕድን ነው፤

፲፭/ “ተቆጣጣሪ” ማለት የማዕድን ሥራ ፈቃዶችን በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት ለመቆጣጠር በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ነው፤

፲፮/“ቴክኒክ ብቃት” ማለት ማንኛውም በማዕድን ሥራዎች ለመሠማራት የሚያመለክት ሰው የሚያቀርበውን የማዕድን ሥራ ፕሮግራም ዕቅድ ለማከናወን በቂ የሆነ ዕውቀት፣ ችሎታና ልምድ ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነው፤

፲፯/ “ቴክኒክ አገልግሎት” ማለት ከማዕድን ሥራዎች ጋር የሚያያዙ ማለትም እንደ ድሪልንግ አገልግሎት፣ የላቦራቶሪ አገልግሎት እና የመሳሰሉትን ሥራዎች ለማከናወን የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለው ኢትዮጵያዊ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለማዕድን ሥራ ፈቃዶች

### ምዕራፍ አንድ

### ስለፈቃድ ማመልከቻዎች

10/“license application fee” means a payment conducted by any applicant for registration of his application for mining operations;

11/“block” means one portion of area acquired by partitioning the total license area in accordance with Article 14 of this Regulation;

12/“performance report” means a document prepared by the licensee in accordance with the license agreement which contains detail technical and financial activities of his mining operation and the result thereof;

13/“Proclamation” means Mining Operation Proclamation No. 678/2010 (as amended);

14/“samples of mineral” means minerals which are not in commercial volume and taken from natural bulk for the purpose of conducting research, laboratory testing, and for market promotion subject to processing as well as for other objectives, as appropriate;

15/“supervisor” means a person authorized by the Licensing Authority, to supervise and administer mining operations, pursuant to the Proclamation and this Regulation;

16/“technical competence” means a document submitted by any person who applies for mining operation that demonstrates applicant’s knowledge, skills and experience to carry out his mining operation in accordance with the proposes work program;

17/“technical service” means a provision of services associated with a mining operations like drilling or laboratory services carried out by an Ethiopian who possess the required certificate of technical competency.

## PART TWO

## LICENSES OF MINING OPERATIONS

### CHPTER ONE

### APPLICATIONS FOR LICENCES

፫. ለቅኝት ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

የቅኝት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፦

፩/ አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡

ሀ) ሙሉ ስሙን፣ ፆታውን፣ ዕድሜውን፣ ዜግነቱን፣ የትውልድ ቦታውን እና የመታወቂያውን ቅጂ፣

ለ) ሙያውን፣

ሐ) የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻውን፣

መ) ፈቃድ የተጠየቀበትን የማዕድን ዓይነት እና የማዕድን ሥራው ሊካሄድ የታሰበበትን ሥፍራ የሚያሳይ ቀላል ጂኦሜትሪያዊ ቅርጽ ያለው አመልካች ካርታ፣

ሠ) ፈቃዱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ አመልካቹ ሊያከናውን ያሰበው የሥራ ፕሮግራም እና ሊያወጣ ያቀደውን የወጪ መጠን፣

ረ) የቅኝት ሥራው በመሬት ገጽታ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም የማያደርስ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣

ሰ) የሥራ ፕሮግራሙ የተዘጋጀው አመልካቹ ቀጥሮ በሚያሰራው ባለሙያ ከሆነ የአዘጋጁ ባለሙያ ሙሉ ስም፣ ሙያው፣ የመታወቂያ ቅጂ እና እንደ አግባቡ የሥራ ውል፣

ሸ) የሥራ ፕሮግራሙ የተዘጋጀው በአማካሪ ከሆነ በወቅቱ የታደሰ የአማካሪው የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር እና የማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት ቅጂ፣

ቀ) ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ዝርዝር ማስረጃዎች፡፡

፪/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ፦

ሀ) ስሙን፣ ዜግነቱን እና ካፒታሉን፣

ለ) የዋና መሥሪያ ቤቱን አድራሻ እና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የወኪሉን ስምና አድራሻ፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (መ)፣ (ሠ)፣ (ረ)፣ (ሰ)፣ እና (ሸ) የተጠቀሱ ዝርዝር ማስረጃዎች፣

መ) ትክክለኛነታቸው አግባብ ባለው መስሪያ ቤት ተረጋግጦ በአመልካቹ የሚቀርቡ የሚከተሉት ሰነዶች፦

3. **Applications for Reconnaissance License**

Application for reconnaissance license shall be attached with the following particulars:

1/ where the applicant is a natural person:

a) his full name, sex, age, nationality, place of birth and copy of identification card;

b) profession;

c) place of residence and address;

d) a simple geometrical map that indicates the proposed mining area with a type of mineral subject to a license;

e) intended work program and expenditure during the license period;

f) evidence that shows the reconnaissance work could cause damage to the surface of the earth or not;

g) where the work program is prepared by the applicant's employee, the full name, profession, copy of Identity Card of the employee who prepared the program and employment contract as the case may be;

h) where the work program is prepared by the consultant; renewed trade license, Tin Number, copy of a certificate of professional competence for consultancy service; and

i) other relevant documents the Licensing Authority may determine by directives;

2/ Where the applicant is a legal person :

a) its name, nationality, and capital;

b) address of its head office, name and address of its representative in Ethiopia;

c) information's specified in paragraph (d), (e), (g), (h) and (i) of sub-article (1) of this Article; and

d) the following documents duly certified by the appropriate government organization:

(፩) ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመሥረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂ፣

(፪) በአመልካቹ ድርጅት ስም ለመፈረም ሥልጣን የተሰጠውን የተፈጥሮ ሰው ስምና የመታወቂያ ቅጂ፡፡

፬. <u>ለምርመራ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

የምርመራ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፡

፩/ አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፫ (፩) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ቀ) የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎችን ፊደል ተራ (ረ) በስተቀር፣

ለ) አመልካቹ የምርመራ ፈቃድ ለመጠየቅ መሠረት ያደረገው የቅኝት ፈቃድ ካለው የፈቃዱን መለያ ቁጥር፣

ሐ) ፈቃድ ስለተጠየቀበት ማዕድን እና ሥፍራ ከዚህ በፊት የሚታወቅ የጂኦሳይንስ መረጃ ዘገባን ጨምሮ ፈቃዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ አመልካቹ ሊያከናውን ያሰበውን የሥራ ፕሮግራም እና ሊያወጣ ያቀደውን የወጪ መጠን፣

መ) በአካባቢ እና በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርስ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ እና መልሶ ማልማት ዕቅድ ሰነድ፣

ሠ) የአመልካቹን የቴክኒክ ብቃትና ልምድ የሚያሳይ መግለጫ፣

ረ) አግባብ ባለው የመንግሥት መስሪያ ቤት የተረጋገጠ የአመልካቹ የፋይናንስ ሁኔታ መግለጫ፣

ሰ) ያመለከተውን ሥፍራ የሚያሳይ የጂኦግራፊክ ኮኦርዲኔት ማስረጃ፣

ሸ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ (፩) ፊደል ተራ (መ) (፩) እና (፪) መሰረት የተዘጋጀ ካርታ፣

፪/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ፡

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፪) የተዘረዘሩትን መረጃዎች፣

(1) copies of its memorandum and articles of association;

(2) the name and evidence of the natural person who is designated to sign on behalf of the applicant organization;

4. <u>**Application for an Exploration Licenses**</u>

Application for an exploration licenses shall be attached with the following particulars:

1/ where the applicant is a natural person:

a) particulars stated under paragraph (a) to (i) of Article 3(1) of this Regulation, except the particular stated under paragraph (f);

b) the applicant's reconnaissance license number, if any, on which the application is based;

c) a geo-science information known to applicant regarding the minerals and the area for which the license is requested including a work program and proposed expenditure during the term of the license;

d) documents showing environmental and natural resource impact assessment and restoration plan;

e) explanation showing the applicant's technical competence and experience;

f) the applicant financial situation which is approved by the competent government organ;

g) evidence showing the geographical coordinates of the area subject to an application;

h) a map prepared in accordance with paragraph (d) numbers (1) and (2) of sub-article (1) of Article 6 of this Regulation;

2/ where the applicant is a legal person:

a) particulars specified under Article 3(2) of this Regulation;

ለ) ያለፉት ሦስት ዓመታት የሂሣብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫዎች እና የኦዲት ሪፖርት ቅጂዎች፣

ሐ) ድርጅቱ በቦርድ የሚተዳደር ከሆነ ትክክለኛነታቸው አግባብ ባለው የድርጅቱ ኃላፊ ተረጋግጦ የሚቀርቡ የሚከተሉት ሰነዶች፣

(፩) የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት የመጨረሻውን ቅጂ፣

(፪) የዳይሬክተሮች ቦርድ የአባላት ስም፣ አድራሻና ዜግነት፡፡

## ፭. ይዞ ለመቆየት ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

ይዞ የመቆየት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፣

፩/ አመልካቹ ይዞ የመቆየት ፈቃድ ለመጠየቅ መሠረት ያደረገው የምርመራ ፈቃድ መለያ ቁጥር፣

፪/ ይዞ የመቆየት ፈቃድ የተጠየቀበትን ሥፍራ የጂኦግራፊክ ኮኦርዲኔቶች አመልካች ካርታ፣ .

፫/ በምርመራ ሥራ የተረጋገጠውን የማዕድን ክምችት መጠን የሚያስረዳ አጠቃላይ የቴክኒክ ዘገባ፣

፬/ ክምችቱን ወደ ምርት ለማሸጋገር ያልተቻለበትን መልካም ያልሆነ የገበያ ሁኔታ፣ የማበልፀጊያ ቴክኖሎጂ አለመኖሩን ወይም ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚስረዱ መረጃዎች፣

፭/ የአዋጭነት ጥናት ዘገባ፣

፮/ ይዞ ለመቆየት በተጠየቀበት ዘመን ውስጥ ሊወሰዱ የታቀዱ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃዎች ዝርዝርና የጊዜ ሰሌዳ፣

፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፬ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃዱ ጸንቶ እንዲቆይ የሚፈለግበትን ጊዜ፡፡

## ፮.ለአነስተኛ ወይም ለከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

፩/ አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡-

b) copies of the balance sheets, profits and loss statements and auditor's reports for the previous three years,

c) where the entity administered by Board of Directors, the following documents duly certified by the appropriate head of such entity:

(1) copy of the latest annual report of the board of directors,

(2) name, address and nationality of board of directors.

## 5. Application for Retention License

Application for retention license shall be attached with the following particulars:

1/ the identification number of the applicant's exploration license on which the application is based;

2/ the geographic coordinates of the proposed retention license, and an indicative map;

3/ the general technical information of the potential mineral reserve verified during exploration stage;

4/ justifications for adverse market conditions, unavailable processing technologies or other economic factors that prevent to develop the mineral deposit;

5/ feasibility study report;

6/ possible alternative measures to be undertaken during the retention period and their time table;

7/ subject to the provisions of Article 24 (1) of the Proclamation, the period for which the license is sought.

## 6. Application for a Small or large Scale Mining License

An application for a small scale or large scale mining license shall be attached with the following particulars:

1/ where the applicant is a natural person:

ሀ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፫ (፩) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ቀ) የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎችን፣ ከፊደል ተራ (ረ) በስተቀር፣

ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ (፩) ፊደል ተራ (ረ) እና (ሰ) የተዘረዘሩት መረጃዎች፣

ሐ) አመልካቹ የምርት ፈቃድ ለመጠየቅ መሠረት ያደረገው የምርመራ ፈቃድ ካለው የፈቃዱን መለያ ቁጥር፣

መ) የአዋጭነት ጥናት ሰነድ፣

ሠ) የማዕድን ማምረት ሥራው በተፈጥሮ አካባቢና በማህበረሰብ ላይ ስለሚያስከትለው ተጽዕኖ የግምገማ ጥናት ሪፖርት፣

ረ) ሊከናወን ስለታሰበው የልማትና ምርት ዕቅድ እና ሌሎች ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በመመሪያ የሚወስናቸው መረጃዎች፡፡

፪/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ፦

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሐ)፣ (መ)፣ (ሠ) እና (ረ) የተዘረዘሩት መረጃዎች፣

ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፩) ፊደል ተራ (መ)፣ (ሰ) ፣ (ሸ) እና ንዑስ አንቀጽ(፪) ፊደል ተራ (ሀ) ፣ (ለ) እና (መ) የተዘረዘሩት መረጃዎች፣ እና

ሐ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ (፪) ፊደል ተራ (ለ) የተዘረዘሩትን መረጃዎች፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (መ) የተመለከተው የአዋጭነት ጥናት ሰነድ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦

ሀ) አግባብ ባለው የወሰን ቅየሳ ላይ ተመሥርቶ ፈቃዱ የተጠየቀበት ሥፍራ ወሰኖች፣ መታጠፊያ ጂኦግራፊያዊ ኮኦርዲኔቶችና በእነሱም መካከል ያለውን ርቀት የሚያመለክት በስኬል የተዘጋጀ ካርታ፣

ለ) ኦፊሴላዊ በሆነ የወሰን ቅየሳ ላይ ተመሥርቶ ሥፍራውን ለመለየት የሚያስችሉ ፈቃድ በተጠየቀበት ክልል ውስጥ እና ቢያንስ ከወሰኑ በ ፭፻ ሜትር ርቀት የሚገኙ ዐቢይ ምልክቶችን፣ ሕንፃዎች፣ የመሬት አቀማመጥ፣ የመሠረተ ልማት አውታሮችና ሌሎች ገጽታዎችን የሚያሳይ አግባብ ባለው መስፈርት የተሠራ ካርታ፣

a) particulars stated under paragraph (a) to (i) of Article 3(1) of this Regulation, except the particular stated under paragraph (f);

b) information specified under paragraph (f) and (g) of Article 4(1) of this Regulation;

c) the applicant's exploration license number on which the application is based, if any;

d) feasibility study document;

e) environmental and social impact assessment reports of the mining operation;

f) proposed development program and other information determined by the directives of the Licensing Authority.

2/ Where the applicant is a legal person:

a) the information's specified under paragraph (c) , (d), (e) and (f) of sub-article (1) of this Article;

b) the information's specified under paragraph (d), (g) and (h) of sub-article (1) and paragraph (a), (b) and (d) of sub-article (2) of Article 3 of this Regulation;

c) the information's specified under paragraph (b) of Article 4 (2) of this Regulation.

3/ The feasibility study document specified under paragraph (d) of sub-article (1) of this Article shall include the following:

a) a plan of the proposed license area, at an appropriate scale, indicating the geographical coordinates of the turning points along its boundaries and the map which shows the distance between them;

b) a map of the proposed license area at an appropriate scale, indicting the geographical coordinates within the license area and at least 500 meters along its official boundary survey, and showing major land marks, buildings, infrastructures, topographic and other physical features;

ሐ) የማዕድኑ ፊዚካል፣ ሚነራሎጂካል፣ ጂኦቴክኒካል ባሕርይ ጨምሮ የክምችቱ ዝርዝር ሁኔታ ጥናት፣

መ) ማዕድኑን ለማምረት የሚያስችል ተቀባይነት ያለው የማምረት ሙከራ ቴክኖሎጂውን፣ ዝርዝር የጥናት ውጤት ጨምሮ ማዕድኑን ለማምረት የታቀደበት ዘዴ፣

ሠ) የተረጋገጠውንና የተገመተውን የማዕድን ክምችት መጠን እና ክምችቱን ዘላቂ በሆነ መንገድ ለማምረት ፈቃዱ ጸንቶ እንዲቆይ የሚፈለግበትን ጊዜ፣

ረ) የገበያ ሁኔታን፣ በየዓመቱ ለማምረት የታቀደውን የምርት መጠን፣ የሽያጭ ገቢን፣ የካፒታልና የሥራ ማስኬጃ ወጪን፣ የእርጅናና ሌሎች ተቀናሾችን እንዲሁም የሚገመተውን ትርፍና የገንዘብ ፍሰት የሚያሳይ የተሟላ ጥናት፣

ሰ) የአመልካቹ ተቋማዊ መዋቅር፣

ሸ) የሚያስፈልጉ የመሠረተ ልማት አውታሮች ዝርዝር፣

ቀ) የቅጥርና የሥልጠና ፕሮግራም አጭር መግለጫ፡፡

፯. <u>የልዩ አነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

የልዩ አነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፣

፩/ አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፣

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) የተዘረዘሩትን፣

ለ) ፈቃድ ለተጠየቀበት ቦታ የአካባቢ እና የተፈጥሮ ሀብት ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ፣

ሐ) በፈቃድ ዘመኑ በሚያከናውነው ሥራ በአካባቢ እና የተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት መልሶ ለማልማት ያቀደውን የወጪ መጠን፣

መ) በፈቃድ ዘመኑ ሊያከናውነው ያቀደውን የሥራ ፕሮግራም እና ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ የሚውል የገንዘብ አቅም መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ፣

c) details of the reserve including physical, mineralogical, geotechnical characteristics of the minerals;

d) the proposed production method including detail study for acceptable and good trial production technology;

e) proved, estimated and inferred reserves of the deposit, and the period for which the license is sought to mine the reserve in sustainable manner;

f) comprehensive study of market conditions, the planned amount of annual production and sales revenues, capital and operating expenditures, depreciations and other deductibles and estimated profit and cash flow;

g) the applicant's organizational structure;

h) details of essential infrastructures;

i) program summery of employment and training.

7. **<u>Application for Special Small Scale Mining License</u>**

Application for special small scale mining license shall be attached with the following particulars:

1/ where the applicant is natural person:

a) information specified under paragraph (a), (b), (c) and (d) of Article 3 (1) of this Regulation;

b) environmental and natural resource impact assessment document with respect to the area which the license is requested for;

c) intended amount of expenditure for the environmental and natural resource impact restoration work during the license period;

d) information with regard to the intended work program to be discharged during the license period and his financial position to execute the same;

ሠ) ቀደም ሲል የወሰደው የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ካለው ዋናውን ከአንድ ቅጂ ጋር፡

፪/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ፡

ሀ) ስሙን፣ ዜግነቱን፣ የሕግ አቋሙን እና አድራሻውን፣

ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፩) ፊደል ተራ (መ) እና ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (መ) የተዘረዘሩትን፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ) እና (ሠ) የተዘረዘሩትን፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች አግባብ ያላቸው መረጃዎች፡፡

## ፰. ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፡

፩/ አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡

ሀ) ሙሉ ስሙን፣ ዜግነቱን፣ ፆታውን፣ ዕድሜ እና አድራሻውን፣

ለ) ፈቃድ የተጠየቀበት ማዕድን የሚገኝበትን ሥፍራ፣

ሐ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በአግባቡ ያስፈልጋሉ ብሎ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መረጃዎች፣

፪/ አመልካቹ የአነስተኛ እና ጥቃቅንኢንተርፕራይዝ ከሆነ፡

ሀ) ስሙን፣ አድራሻውን እና ዜግነቱን፣

ለ) አግባብ ባለው የአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ሕግ መሠረት የተመዘገበና የንግድ ሥራ ማካሄድ የሚችል መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) የተዘረዘሩትን መረጃዎች፡፡

e) the original and a copy of his previous artisanal mining license.

2/ where the applicant is a legal person:

a) its full name, nationality, legal form and address;

b) information specified under paragraph (d) of sub-article (1) and paragraph (d) of sub-article (2) of Article 3 of this Regulation;

c) information specified under paragraph (b), (c), (d) and (e) of sub-article 1 of this Article.

3/ other relevant documents determined by the directive of the Licensing Authority.

## 8. Application for an Artisanal Mining License

Application for an artisanal mining license shall be attached with the following particulars:

1/ where the applicant is a natural person:

a) his full name, nationality, sex, address and age;

b) location of the minerals for which the license is requested;

c) other relevant documents determined by the c...ective of the Licensing Authority;

2/ where the applicant is small and micro enterprise:

a) his name, address and nationality;

b) evidence that demonstrate as it registered as small and micro enterprise in accordance with relevant law and eligible to carry on trade pursuant to commercial law;

c) information specified under paragraph (b) and (c) of sub-article (1) of this Article.

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለፈቃድ አሰጣጥ

### ፱. ማመልከቻን ስለመመዝገብ

፩/ ማንኛውም የፈቃድ ማመልከቻ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለዚህ ዓላማ ባዘጋጀው ፎርም ተሞልቶ ሲቀርብ ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫፣ ፬፣ ፭፣ ፮፣ ፯ እና ፰ የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ከማጣራቱ በፊት ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው መዝገብ ላይ እንደ አቀራረቡ ቅደም ተከተል ይመዘገባል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ማመልከቻ የቀረበ እንደሆነ ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (፪) የተመለከተው ጊዜ ሲያበቃ አመልካች የምዝገባ ክፍያ እንዲፈጽም አድርጎ ማመልከቻው የተመዘገበበትን ቀን፣ ሰዓትና ቁጥሩን የሚገልጽ የማዕድን ካዳስተር ምዝገባ ማረጋገጫ ለአመልካች ይሰጠዋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የተፈጸመ የማመልከቻ ምዝገባ ብቻውን አመልካቹን ፈቃድ ለማግኘት ብቁ አያደርገውም፡፡

፬/ ዝርዝር ሁኔታው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሰረት የፈቃድ ማመልከቻዎች ለሕዝብ ክፍት ይደረጋሉ፡፡

፭/ ተመዝግቦ በፈቃድ ሂደት ላይ ያለ ማንኛውም የፈቃድ ማመልከቻ ሂደቱ ከተጀመረ በኋላ አመልካቹ ጉዳዩን ሳይከታተል ቢቀር ወይም እንዲያሟላ የተጠየቀውን የጎደለ ማስረጃ ሳያሟላ ከሁለት ወር በላይ ከዘገየ የፈቃድ ጥያቄውን በራሱ ፈቃድ እንደተወ ተቆጥሮ የፈቃድ ሂደቱ ይቋረጣል፡፡

### ፲.መቃወሚያዎችን ስለማቅረብ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (፪) መሠረት ማንኛውም ሰው የተጠየቀው ፈቃድ እንዳይሰጥ መቃወሚያውን በጽሁፍ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ተቃውሞውን ውድቅ አድርጎ የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻውን ካጸደቀው ውሳኔውን በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፱ (፪) መሠረት ለዚህ ጉዳይ በተዘጋጀ የማዕድን ካዳስተር መረጃ መዝገብ ላይ ያሰፍረዋል፤ አመልካቹም በመዝገቡ ላይ ይፈርማል፡፡

## CHAPTER TWO

## ISSUANCE OF LICENSE

### 9. Registration, of Applications

1/ Any application for a license filled and submitted in form prepared by the Licensing Authority for such purpose, shall be registered in the registry prepared for same in their order of reception before examining the fulfillment of the information specified under Article 3, 4, 5, 6, 7 and 8 of this Regulation.

2/ When application is submitted pursuant to sub-article (1) of this Article the Licensing Authority shall, after the laps of the period specified under Article 14(2) of the Proclamation, cause payment of registration fee and provide the applicant with the approved mineral cadastre registry which specifies the date, time and number of registration.

3/ The registration of application conducted pursuant to sub-article (1) and (2) of this Article merely shall not make the applicant eligible for a license.

4/ The registry shall be open to the public in accordance with directive to be issued by the Licensing Authority for inspection.

5/ Any application registered shall be considered abandoned by the applicant and as a result the licensing process shall be terminated, if the applicant fails to follow up the licensing process or fails to provide the required information for more than two months.

### 10. Lodging of Objections

1/ Any person may file a written objection against the grant of such license in accordance with Article 14(2) of the Proclamation.

2/ If the Licensing Authority rejects the objection and approves the application, it shall enter such decision in a registry of cadastre kept for same purpose pursuant to Article 9(2) of this Regulation; and the applicant shall sign on the register.

## ፲፩. ፈቃድን ስለመስጠት፣ ስለመመዝገብና ስለማስታወቅ

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ የተጠየቀውን ፈቃድ ይሰጣል፡

ሀ) ማመልከቻ ቀርቦ ፈቃድ የተጠየቀበት ሥፍራ አስቀድሞ ፈቃድ ያልተሰጠበት እና በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች ያልተከለከለ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) ፈቃድ የተጠየቀበትን ሥፍራ የጂኦግራፊያዊ ኮኦርዲኔትና ማዕድኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው ጋዜጦች አማካይነት በአመልካቹ ወጪ እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (፪) ድንጋጌ መሠረት በሰባት ቀናት ውስጥ በማመልከቻው ላይ መቃወሚያ ካልቀረበ፣

ሐ) አመልካቹ ዋናውን የንግድ ፈቃድ ምስክር ወረቀት እና የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ካቀረበ፣

መ) በማመልከቻው ላይ የቀረቡት መረጃዎች ትክክለኛና ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን ካረጋገጠ፣

ሠ) አመልካቹ በሥራ ፕሮግራሙ የተመለከቱትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል የቴክኒክ ችሎታና ልምድ እንዲሁም የገንዘብ አቅም እንዳለው እና የተጠየቀው ፈቃድ የሚያስከትላቸውን ሌሎች ግዴታዎች ለመወጣት የሚችል መሆኑን ካረጋገጠ፣

ረ) አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፮ መሠረት የፈቃድ ክፍያ መክፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካቀረበ፣

ሰ) የተጠየቀው የማዕድን ማምረት ፈቃድ ከሆነ የፈቃድ ክልሉ ሁኔታና አቀማመጥ በአዋጁ ድንጋጌ መሰረት መሆኑን ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በቅድሚያ በቦታው ላይ በመገኘት ካረጋገጠ፡፡

፪/ ዝርዝር ሁኔታው በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተሰጡ ፈቃዶችን ለሕዝብ ክፍት ያደርጋል፡፡

## 11. Grant, Registration and Notification of License

1/ The Licensing Authority after verifying the fulfillment of the following conditions shall grant the requested license:

a) where the area for which application is lodged for license is not subject to another licensee and not prohibited by any other appropriate laws;

b) where the geographical coordinates and descriptions of minerals of an area subject to an application published on news papers which have wider circulation by the expense of the applicant and no objection is filed within 7 days as specified under Article 14 (2) of the Proclamation;

c) where the original certificate of business license and a Taxpayers Identification Number (TIN) is submitted;

d) information submitted in connection with the application are verified to be correct and acceptable;

e) where the applicant has demonstrated that he has the necessary technical capability and experience to carry out undertakings specified under the work program and financial resources to execute the work program and to meet any other obligations emanated from the license requested;

f) the applicant, pursuant to Article 46 of this Regulation, submit all information that proves the payment of prescribed license fee;

g) where the application is for mining license, the licensing authority primarily ascertain by physical appearance that the topographic conditions and coordinates of the license area are in accordance with the Proclamation.

2/ The registry of the granted license shall be opened to the public for inspection in accordance with directive to be issued by the Licensing Authority.

፫/ ማንኛውም ሰው ፈቃድ የተሰጠባቸውና ማመልከቻ የቀረበባቸውን ቦታዎች የሚያሳይ በመለያ ቁጥር የተመዘገበ የመረጃ ካርታ እንዲሰጠው ሲጠይቅ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፯ የተመለከተውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም የካርታውን ቅጂ ማግኘት ይችላል፡፡

## ፲፪.በጨረታ የፈቃድ አሰጣጥ

፩/ በጨረታ ፈቃድ የሚሰጠው፡

ሀ) የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ (፬) እና የዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ (፩) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተረጋገጠ መረጃና የማዕድን ክምችት ምልክት እንዳላቸው ተለይተው የታወቁ የከበሩ ማዕድናት፣ የብረት ነክና እንደ አስፈላጊነቱ የሌሎች ማዕድናት ቦታዎች የማዕድን ምርመራ እና ማምረት ሥራ ፈቃድ ሲሆን፣

ለ) በጨረታ ፈቃድ ለመስጠት የማዕድኑ ዓይነትና ቦታው ተለይቶ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሲወሰን፣ እና

ሐ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጨረታ አወዳድሮ ፈቃድ ለመስጠት የጨረታ ማስታወቂያ ሲያወጣ እና ከአንድ በላይ አመልካቾች በተወሰነው የጊዜ ገደብ ማመልከቻዎች ሲያቀርቡ፡፡

፪/ ለጨረታ የሚቀርብ ሰነድ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

ሀ) የአመልካቹን የቴክኒክ ሥራ ዕቅድ፣ ለሥራው ሊያወጣ ያሰበውን የገንዘብ መጠን፣ የፋይናንስ ሁኔታ መግለጫ፣ የሥራ ልምድና ብቃት፣

ለ) አመልካቹ ለግዴታዎቹ መፈጸም ማረጋገጫ የሚሆን ለመጀመሪያው ዓመት ከመደበው በጀት ፳፭% የሚሆነውን ስለማስያዙ ከፋይናንስ ተቋማት ዋስትና ማቅረብ፡፡

፫/ ለጨረታ የቀረቡ ማመልከቻዎች ምርጫ የሚካሄደው በመመሪያ በሚወሰነው መስፈርት መሠረት ሆኖ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ከፍተኛ ውጤት ላገኘው አመልካች ፈቃድ ይሰጣል፡፡

3/ Any person may, upon request and payment of the service fee specified under Article 47 of this Regulation, get the copy of the registered and numbered map of the area which specifies the area for which application is lodged or license is granted.

## 12. Granting License through competitive bid

1/ License may be granted through competitive bid:

a) without prejudice to Article 13 (4) of the Proclamation and Article 11(1) of this Regulation, when it is an exploration and mining licensee over the area in which the existence of deposit of precious minerals, metal and as the case may be a deposit of other minerals, is discovered;

b) when the Licensing Authority decides that the mining area in which the minerals discovered shall be licensed through competitive bid;

c) when the Licensing Authority decides to grant license through competitive bidding and more than one applicant lodge application within the determined period of time.

2/ A bid document shall be attached with the following:

a) document showing the applicant's technical and operational plan, money allocated for operation, financial situation, experience and competence;

b) a guarantee from financial institutions which accounts for 25% of the proposed first year budget for performance of obligation.

3/ The selection of application lodged for bid shall be conducted in accordance with the criteria determined by directive and the Licensing Authority shall grant a license for the applicant who scores the highest result.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ) መሰረት በባንክ የተያዘው የዋስትና ገንዘብ በጨረታው ለተሸነፉ አመልካቾች ወዲያውኑ የሚመለስ ሲሆን ጨረታውን ላሸነፈው አመልካች የመጀመሪያ ዓመት የሥራና የወጪ ግዴታውን መወጣቱ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሲረጋገጥ ይመለሳል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ቢኖርም ባለፈቃዱ ግዴታውን ካልተወጣ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ይሆናል፡፡

፮/ በጨረታ ማስታወቂያው መሠረት የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ከሆነ፣ በድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ካልተወሰነ በስተቀር ጨረታው ተሰርዞ የፈቃድ አሰጣጡ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ እስከ ፲፩ በተመለከቱት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## ፲፫.ፈቃድ ስለመከልከል

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በሚከተሉት ምክንያቶች ፈቃድ እንዳይሰጥ ሊከለክል ይችላል፡

ሀ) የፈቃድ ማመልከቻው ወይም ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው የቀረቡት መረጃዎች ያልተሟሉ ናቸው ብሎ ከወሰነ፣

ለ) አመልካቹ ያቀረበው የሥራ ፕሮግራም፣ ለሥራው የተመደበ የወጪ መጠን እና የልማትና የምርት ፕሮግራም ግዴታዎች ተቀባይነት ካላገኙ፣

ሐ) ፈቃድ የተጠየቀበት ሥፍራ ተቃውሞ የቀረበበት እንደሆነና ተቃውሞው ተቀባይነት ካገኘ፣

መ) ተቃውሞ የቀረበበት አመልካች ማመልከቻውን ማረም ወይም የጎደለውን ማሟላት ካልቻለ፣

ሠ) ተቃውሞ የቀረበበት አመልካች የቀረበበትን ተቃውሞ በሰባት ቀናት ጊዜ ውስጥ ማስተባበል ካልቻለ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፈቃድ የማይሰጥ ከሆነ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ምክንያቶቹን ለአመልካቹ በ፲፭ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

4/ The guarantee provided pursuant to sub-article (2) (b) of this Article shall immediately be returned for those who lost the bid; provided, however, that the winner's guarantee shall be returned, when the Licensing Authority believes that the obligation of expenditure and work program to which he proposed for his first year mining operation has been fulfilled.

5/ Notwithstanding the provision of sub-article (4) of this Article, if the applicant fails to meet his proposed obligations the guarantee money shall be paid to government account.

6/ If only one bidder appears the bidding process shall be cancelled, unless the Licensing Authority decides for second-bid, and the process of granting license shall be conducted in accordance with Article 9 to 11 of this Regulation.

## 13. Refusal to Grant License

1/ The Licensing Authority may refuse to grant a license by the following reasons:

a) if the application or related information supplied in connection with the license are materially incomplete;

b) if the work program submitted, the amount of expenditure allocated for the work program and guarantee of financial posit' , or development and production program obligations are not acceptable;

c) if the proposed license area is subject to an objection and the Licensing Authority uphold the objection;

d) if the applicant, against whom an objection filed, failed to amend or complete deficiencies of his application;

e) if the applicant, against whom an objection filed, failed to rebut the objection within seven days.

2/ If the Licensing Authority refuses to grant a license pursuant to this Article, it shall so notify in writing, within 15 days, by stating the reasons for its decision.

## ፲፬. ስለፈቃድ ክልሎች ስፋት

፩ ለአመልካች የሚሰጠው የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ከአንድ ብሎክ በላይ እና እንደሁኔታው በተለያዩ ሥፍራዎች የሚገኝ የፈቃድ ክልልን ሊይዝ የሚችል ሆኖ አንድ ባለፈቃድ ሊይዝ የሚችለው የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ ዝርዝር በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ የፈቃድ ብሎክ ክልል ሥር ሊሸፈን የሚችለው የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ እንደሚከተለው ይሆናል፡

ሀ) ለቅኝት ፈቃድ ፶ ካሬ ኪሎ ሜትር፡

ለ) ለምርመራ ፈቃድ ፳ ካሬ ኪሎ ሜትር፡

ሐ) ይዞ የመቆየት ፈቃድ ፻ ሺ ካሬ ሜትር፡

መ) ለባሕላዊ የማዕድን ሥራ ፈቃዶች ፭ ሺ ካሬ ሜትር፡

ሠ) ለአነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪያልና የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ፻ ሺ ካሬ ሜትር፡

ረ) ለከፍተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ እና የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ፪፻ ሺ ካሬ ሜትር፡

ሰ) ለከበሩ፡ በከፊል ለከበሩ፡ ለብረት ነክ እና ለሌሎች ማዕድናት የአነስተኛና የከፍተኛ ደረጃ ማምረት ሥራ ፈቃዶች አንድ ካሬ ኪሎ ሜትር፡፡

፫/ የባሕላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በአንድ ጊዜ ከሁለት በላይ ፈቃድ እና ጠቅላላ ስፋቱ ከ ፲ ሺ ካሬ ሜትር የበለጠ ቦታ አይሰጠውም፡፡

፬/ ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ቀደም ሲል በተሰጠው የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ቦታ ላይ የተሻለ የማምረት ሥራ መስራቱ ከተረጋገጠ በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት ተጨማሪ መሬት ሊሰጠው ይችላል፡፡

፭/ የአነስተኛ እና የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ እንደ ማዕድኑ ዓይነት በመመሪያ የሚወሰን እና በጥናት በተረጋገጠው የክምችት መጠን ሆኖ ከ ፸፭ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሊመረት የሚችል የማዕድን ክምችት ሊይዝ ከሚችለው የፈቃድ ክልል ስፋት በላይ መሆን የለበትም፡፡

## 14. Size of License Area

1/ The maximum area to be granted for an applicant may cover more than one block and as the case may be it might include different license areas; provided, however that the maximum area to be held by a single licensee shall be as determined in a directive.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, the maximum area to be covered by a single block shall be the following:

a) 50 $km^2$ for a reconnaissance license;

b) 20 $km^2$ for exploration license;

c) 100,000 $m^2$ for retention license;

d) 5,000 $m^2$ for artisanal mining license;

e) 100,000 $m^2$ for the small scale industrial and construction minerals mining license;

f) 200,000 $m^2$ for large scale industrial and construction mineral mining license;

g) one square kilo meter for small scale and large scale mining license for precious, semi-precious, metallic and other minerals.

3/ An artisanal mining licensee shall not be granted with more than two licenses and an area exceeding 10,000 $m^2$ at a time.

4/ Where the mining activity of the A special small scale mining licensee granted license in the previous artisanal mining license area, if demonstrates good production performance, additional area may be granted as determined in the directive.

5/ The maximum areas of small and large scale mining license might be determined by directive to be issued based on the type of the mineral; provided, however, it would not be more than a license area proved to have deposit of mineral reserve which could be mined in not more than 75 years.

## ፲፭.ምትክ የፈቃድ ቅጂ ስለመስጠት

፩/ ማንኛውም ፈቃዱ የጠፋበት፣ የተበላሸበት፣ የተሰረቀበት፣ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጭ የሆነበት ባለፈቃድ ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን በጽሁፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣንም የቀረበው ጥያቄ ትክክለኛ መሆኑን በማጣራትና በማረጋገጥ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፯ (፪) መሠረት የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ምትክ የፈቃድ ቅጂ ይሰጣል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ፈቃዶችን ስለማደስ፣ ስለማስተላለፍ፤ስለማገድና ስለመሠረዝ

## ፲፮.ስለ ምርመራ ፈቃድ ዕድሳት

፩/ የምርመራ ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ በውሉ የተመለከተው የፈቃድ ዘመን ከመፈጸሙ ከ፷ (ስልሳ) ቀናት በፊት መቅረብና የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡

ሀ) ፈቃዱ መጀመሪያ ሲሰጥ የነበረው መረጃ ወይም ባለፈው ዕድሳት ወቅት በቀረቡ መረጃዎች ላይ የተደረጉ ለውጦች ካሉ፣ የተገኙ ውጤቶችን እና ሌሎች በመመሪያ የሚወሰኑ አስፈላጊ መረጃዎችን ያካተተ ዓመታዊ አጠቃላይ ሪፖርት፣

ለ) ባለፈው የፈቃድ ዘመን የማዕድን ሥራው በአካባቢና በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያስከተለው ተፅእኖ እና መልሶ ለማልማት የተወሰዱ እርምጃዎችን ያካተተ ሪፖርት፣

ሐ) ባለፈቃዱ በቀጣዩ የዕድሳት ዘመን ሊያከናውን ያሰበውን የሥራ ፕሮግራም፣ የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽእኖ ግምገማ፣ የማህበረሰብ ልማት ዕቅድ እና የወጭ መጠን ዕቅድ የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ፣

መ) በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ (፩) መሠረት ከፈቃድ ክልሉ ላይ የሚለቀውን መሬት በመቀነስ እድሳት የተጠየቀበትን ቦታ የሚያመለክት የጂኦግራፊክ ኮኦርዲኔት የያዘ መረጃ፣

## 15. Replacement of Copies of License

1/ The licensee may apply in writing to the Licensing Authority for replacement of a license which has been lost, destroyed, dispossessed through theft, or made useless due to various reasons.

2/ The Licensing Authority shall, after investigating and verifying the eligibility of such request, issue the replacement of copy of license to the licensee upon payment of the prescribed service fee, pursuant to Article 47(2) of this Regulation.

## CHAPTER THREE

## RENEWAL, TRANSFER, SUSPENSION AND REVOCATION OF LICENSE

## 16. Renewal of an Exploration License

1/ Application for the renewal of an exploration license shall be submitted made 60 (sixty) days before the end of its terms specified in the license and shall be attached with the following documents:

a) annual summery report which contains information submitted for original license or changes, if any, in the application or during renewal and acquired outputs and other relevant information determined in directive;

b) report including the impact of mining operation resulted to the environment and natural resource in the previous license period and restoration measures taken;

c) the licensee's detail work program, environmental and social impact assessments, development plan and expenditure proposal during each year of the next renewal period;

d) portion of license area be relinquished and geographical coordinate of the license area for which renewal is sought pursuant to Article 22 (1) of the Proclamation;

ሠ) የፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ የተወሰኑ ሌሎች መረጃዎች፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ መሠረት የፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ መቅረብ በነበረበት ጊዜ ካልቀረበ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በ፲፭ ቀን ውስጥ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ማስጠንቀቂያው እንዲደርሰው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፲፭ ቀናት ውስጥ የዕድሳት ማመልከቻ ካልቀረበ የፈቃድ ዘመኑ ካበቃበት ቀን ጀምሮ የፈቃድ መብቱ እንደተቋረጠ ይቆጠራል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (መ) ድንጋጌ መሠረት የሚለቀቀው መሬት ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሌላ አኳኋን ካልተስማማ በስተቀር በብሎክ በብሎክ ሆኖ እያንዳንዱ ብሎክ ከአንድ ካሬ ኪሎ ሜትር ያላነሰና ቀላል ጂኦሜትራዊ ቅርጽ ያለው መሆን አለበት፡፡

፭/ የአዋጁ አንቀፅ ፳፪ (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚከተሉት ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ ከምርመራ ፈቃድ ቦታ ላይ የተወሰነውን ሳይለቅ ፈቃዱ እንዲታደስ ሊፈቅድ ይችላል፦

ሀ) ለሥራው ወሳኝ የሆኑ እንደ ናሙና ምርመራ ውጤት መዘግየት፣ ወሳኝ ማሽነሪዎች በከባድ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ መበላሸት እና ከባለፈቃዱ ቁጥጥር ውጪ የሆኑ ሌሎች ሁኔታዎች ሲከሰቱ፤

ለ) ከሌላ ባለፈቃድ ወይም ሦስተኛ ወገን ጋር በሚፈጠር አለመግባባትና ክርክር ምክንያት በፕሮግራሙ መሠረት መስራት አለመቻል፤

ሐ) ሌሎች በፍትሐ ብሔር ሕጉ ከአቅም በላይ የሆኑ ተብለው የተዘረዘሩት ምክንያቶች ቀጣይነት ባለው እና የጎላ ተፅዕኖ በሥራው ላይ በሚያሳድር መልኩ ሲከሰቱ፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) ወይም (ሐ) የተደነገገው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ከተከሰተ ባለፈቃዱ ችግሩ እንዳይባባስ ተገቢ የሆነውን እርምጃ በመውሰድ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጽሁፍ ማሳወቅና ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

e) other information determined by the directive of the Licensing Authority.

2/ Where the licensee failed to lodged an application for renewal timely pursuant to the provisions of sub-article (1) of this Article, the Licensing Authority submit a written notice to the licensee within 15 days.

3/ Where the licensee fails to submit his renewal application within 15 days after receiving notice pursuant to sub-article (2) of this Article, the license shall be presumed as terminated from the date of its expiry.

4/ The land to be relinquished pursuant to sub-article (1) (d) of this Article shall, unless the Licensing Authority agrees otherwise, be block by block, which is coordinated in a simple geometric form comprised of not less than one square kilometer units.

5/ Without prejudice to the provisions of Article 22 (3) and (4) of the Proclamation, the Licensing Authority after verifying the existence of following force majeure, may allow a renewal of an exploration license without relinquishment of a portion of the license area:

a) prolonged delay of the result of sample test and major break downs of machineries which are decisive for the operation and the occurrence of other similar situations which are beyond the control of the licensee;

b) inability to conduct the operation as per the work program due to disputes with other licensees or any other third party;

c) where the occurrence of events considered as forced majeure under the Civil Code hampers the operation in significant and sustainable manner.

6/ The licensee shall take all reasonable measures to mitigate the impact of the occurrence of force majeure and provide an evidence to prove the occurrence of events specified under paragraph (a), (b) and (c) of sub-article (5) of this Article and notify in writing to the Licensing Authority.

፯/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በማመልከቻው የቀረቡለትን መረጃዎች በማጣራት ተቀባይነት ያላቸው ሆኖ ካገኘ አመልካቹ የፈቃድ ማሳደሻ እና የመሬት ሊዝ ኪራይ መክፈሉን በማረጋገጥ ፴ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ ፲፱ ፪ እና ፫ መሠረት ፈቃዱን ያድስለታል፡፡

## ፲፯. ስለ ይዞ የመቆየት ፈቃድ ዕድሳት

፩/ የይዞ መቆየት ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የፈቃድ ዘመኑ ከመፈጸሙ ከ፺ (ዘጠና) ቀናት በፊት መቅረብና የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ (፬)፣ እና (፭) እና (፮) መሠረት ፈቃዱ መጀመሪያ ሲሰጥ በቀረቡ መረጃዎች ላይ የተደረጉ ለውጦችን፣ የቀጠሉ ሁኔታዎችንና አግባብነት ያላቸው ሌሎች በመመሪያ የሚወሰኑ መረጃዎችን ያካተተ አጠቃላይ ሪፖርት፡

ለ) አመልካቹ በዕድሳት ዘመኑ ማዕድኑን ወደ ልማት እና ማምረት ለማሸጋገር ሊያከናውን ያሰበውን ዝርዝር የሥራ ዕቅድ፡

ሐ) በአዋጁ አንቀጽ ፳፫(፩) መሠረት የተገለፁትን እና በመመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች መረጃዎች፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በማመልከቻው የቀረቡለትን መረጃዎች ካጣራና ተቀባይነት ካገኘ አመልካቹ የተወሰነውን የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያና የመሬት ኪራይ መክፈሉን በማረጋገጥ ፴ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ (፪) መሠረት ፈቃዱን ያድስለታል፡፡

## ፲፰/ ስለ ልዩ አነስተኛ፣ አነስተኛ ወይም ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃዶች ዕድሳት

፩/ ልዩ አነስተኛ፣ አነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የፈቃዱ ዘመን ከመፈጸሙ ከ፩፻፹ ቀናት በፊት መቅረብና የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡

ሀ) ፈቃዱ መጀመሪያ ሲሰጥ ወይም ባለፈው ዕድሳት ወቅት በቀረቡ መረጃዎች ላይ የተደረጉ ለውጦች፣

7/ The Licensing Authority shall, upon payment of the prescribed renewal fees and land lease rental, renew the exploration license in not more than 30 (thirty) days in accordance with Article 19 (2) and (3) of the Proclamation after verifying that the documents attached with the application are acceptable.

## 17. Renewal of Retention License

1/ Application for the renewal of retention license shall be made within 90 days prior to the end of the term of the license and shall be attached with the following documents:

a) the general report which contains any change and condition still prevails in the information submitted during application for the original license pursuant to Article 5 (4), (5) and (6) of this Regulation and other relevant information determined by directive;

b) detail of the proposed work program to develop and mine the minerals during the renewal period;

c) information specified under Article 23(1) of the Proclamation and such other information to be determined by the directives.

2/ The Licensing Authority shall, upon payment of the prescribed fees and land lease rentals, renew the retention license in not more than 30 (thirty) days in accordance with Article 24 (2) of the Proclamation, after verifying that the documents attached with the application are acceptable.

## 18. Renewal of Special Small, Small or Large Scale Mining Licenses

1/ An application for the renewal of special small, small or large scale mining license shall be made 180 days prior to the expiry of the term of the license; and shall attach the following documents:

a) any change in the information submitted during application for the original license or during renewal of same;

ለ) ከልዩ አነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በስተቀር የተረጋገጠውንና ይኖራል ተብሎ የተገመተውን ቀሪውን የማዕድን ክምችት ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት እና የቀጣይ ሥራውን ዕቅድ፣

ሐ) በሚቀጥለው የዕድሳት ዘመን ለማከናወን የታቀደው የምርት ሥራ ፕሮግራም፣ የወጪ ዕቅድና የገንዘብ ፍሰት መግለጫ፣

መ) በውጪ ኦዲተር የተረጋገጠ የባለፈቃዱ ወቅታዊ የፋይናንስ ኦዲት ሪፖርት፣

ሠ) በዕድሳት ዘመኑ የማዕድን ሥራው የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽእኖ ግምገማ ጥናት ሪፖርት፣

ረ) ባለፈው የፈቃድ ዘመን የማዕድን ሥራው በአካባቢና በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያስከተለው ተጽዕኖና መልሶ ለማልማት የተወሰዱ እርምጃዎችን ያካተተ ሪፖርት፡፡

ሰ) ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች እና ቀሪውን የማዕድን ክምችት መጠን ማቅረብ የማይጠበቅባቸውን የማዕድን ዓይነቶች በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው የቀረቡትን መረጃዎች ካጣራና ተቀባይነት ያላቸው ሆኖ ካገኘ፣

ሀ) ባለፈው የማምረት ፈቃድ ዘመን በውሉና በሕግ የተመለከቱትን ግዴታዎች ባለፈቃዱ የተወጣ መሆኑን ካረጋገጠ እና

ለ) አመልካቹ የተወሰነውን የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያና የመሬት ሊዝ ከከፈለ

በአዋጁ አንቀጽ ፳፯፣ ፳፱ እና ፴፫ መሠረት ፈቃዱን ያድስለታል፡፡

## ፲፱.ፈቃድ ስለማስተላለፍ

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፵ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለፈቃድ ወይም ሕጋዊ ወራሽ አስፈላጊውን ሰነድ በማሟላት እና የማመልከቻ መመዝገቢያ ክፍያ በመክፈል የፈቃድ መብቱ እንዲተላለፍለት ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን በጽሁፍ መጠየቅ ይችላል፡፡

b) except the special small scale mining license; detail report indicating the remaining proved, estimated and inferred reserves of the deposit and subsequent plan of operation;

c) the proposed production program, expenditure and cash flow for the next renewal period;

d) the current financial audit report of the licensee confirmed by external auditor;

e) social and environmental impact assessment report for the renewal period;

f) report which shows restoration measure taken to mitigate the impact of the mining activity on environment and natural resource during the previous license period.

g) such other information considered to be relevant and minerals that the amount of reserve deposit is not required shall be determined by the directives.

2/ The Licensing Authority upon examining information submitted with application and accepts them, it shall renew the license in accordance with Article 27, 29 and 33 of the Proclamation:

a) upon verifying that the licensee has discharged his contractual and legal obligation of the previous mining license, and

b) upon the payment of the prescribed renewal and land lease fees by the applicant and

## 19. Transfer of License

1/ Without prejudice to Article 40 of the Proclamation, the licensee or his heirs, by providing all necessary documents and upon payment of application fee, may request in writing the Licensing Authority to transfer his license.

፪/ የምርመራ፣ የአነስተኛ እና የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ መብትን ለመሸጥ ወይም ለመዳረግ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡

ሀ) ፈቃዱን ለመሸጥ ወይም ለመዳረግ የተፈለገው ለተፈጥሮ ሰው ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) የተመለከቱ መረጃዎችን፤

ለ) ፈቃዱን ለመሸጥ ወይም ለመዳረግ የተፈለገው ሰው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፪) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) ፣ (ሐ) እና (መ) የተዘረዘሩትን መረጃዎችን፤

ሐ) ፈቃዱን ለመሸጥ ወይም ለመዳረግ የተደረገ የስምምነት ሰነድ፣

መ) የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን የማምረት ፈቃድን ለመሸጥ ወይም ለመዳረግ የሚቀርብ ማመልከቻ ከሆነ በገቢ ግብር ሕግ መሠረት በአስተላላፊው የአክሲዮን ዋጋ ላይ ተሰልቶ ከሚገኘው ትርፍ ላይ ተገቢው የትርፍ ድርሻ ግብር ስለመፈጸሙ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡፡

፫/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ ፵ መሠረት በዕዳ ለማስያዝ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡

ሀ) በዕዳ መያዣው ተጠቃሚ እንዲሆን የተፈለገው ሰው የተፈጥሮ ሰው ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተዘረዘሩትን መረጃዎች ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፪) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (መ) የተዘረዘሩትን መረጃዎች፤

ለ) ሊሰጥ የታሰበው የዋስትና ዓይነት፣ የመያዣ ውል እና የፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ሌሎች መተማመኛዎች፡፡

፬/ የልዩ አነስተኛ፣ የአነስተኛ እና የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን በአዋጁ አንቀጽ ፵ መሠረት በውርስ ለማስተላለፍ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡

2/ Application for sale or assignment of an exploration, a small scale or large scale mining license, shall be attached with the following:

a) the information specified under paragraph ( a), (b), (c) and (d) of Article 3(1) of this Regulation, if the application to sale or assign the license to a natural person;

b) the information specified under paragraph (a), (b), (c) and (d) of Article 3 (2) of this Regulation, if the application to sale or assign the license to a legal person;

c) contractual agreement of the proposed sale or assignment;

d) evidence of payment of income tax from the net profit which is going to be computed from the transferor's share in accordance with income tax law, if the application to sale or assign small or large scale mining license.

3/ Application for the encumbrance of a small scale or large scale mining license in accordance with Article 40 of the Proclamation shall be attached with the following:

a) wher the proposed beneficiary of such encumbrance is natural person, information required under paragraph (a) and (b) of Article 3(1) or in case the beneficiary is legal person information required under paragraph (a), (b), and (d) of Article 3(2) of this Regulation;

b) the nature, terms and conditions of security interest proposed to be granted including such safeguards specified in the directives issued by the Licensing Authority may require.

4/ Application to transfer a special small scale, small scale and large scale mining license by inheritance in accordance with Article 40 of the Proclamation shall be attached with the following:

ሀ) የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣

ለ) ወራሹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (መ) እንዲሁም ወራሹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፪) (ሀ)፣ (ለ) እና (መ) የተዘረዘሩትን መረጃዎች፡፡

፭/ የባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን በአዋጁ አንቀጽ ፵ በተደነገገው መሠረት በውርስ ለማስተላለፍ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

ሀ) የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ የተዘረዘሩትን መረጃዎች፣

ለ) ፈቃዱ በውርስ የሚተላለፍለት ሰው የፈቃዱን ግዴታዎች አክብሮ ለመፈፀም ግዴታ መግባቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡፡

፮/ ፈቃድ እንዲተላለፍ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ውሳኔ መስጠት የሚችለው የሚከተሉት መረጃዎች ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው መቅረባቸው ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፣

ሀ) ባለፈቃዱ በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ፣ በመመሪያ እንዲሁም በስምምነቱ መሠረት ግዴታዎቹን የተወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) የሚተላለፍለት ሰው ያለው ጠቅላላ የፍቃድ ክልል ይዞታ ስፋት በመመሪያ ለአንድ ሰው ከሚፈቀደው የፈቃድ ክልል ስፋት ጣሪያ በላይ አለመሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ) ፈቃዱ የሚተላለፈው በውርስ ሲሆንና የሚተላለፍለት ሰው ቀደም ሲል የተሰጠው ፈቃድ ካለ ጠቅላላ የፈቃድ ክልሉ ስፋት ከተፈቀደው ጣሪያ በላይ ሆኖ ሲገኝ በውርስ ተሰጥቶ የሚተላለፈውን ፈቃድ የመረጠ ከሆነ፣

መ) ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው በማዕድን ሥራዎች ሕግ፣ የፈቃድ ስምምነቶች እና አግባብ ያለውን የሥራ ፕሮግራም የባለፈቃዱን ግዴታዎች አክብሮ ለመፈጸም ግዴታ ከገባ፡፡

፯/ ከውርስ በስተቀር ማንኛውም የማዕድን ምርመራ ፈቃድ መብት መተላለፍ የሚችለው፣

a) certificate of heir;

b) information required under paragraph (a), (b), (d) of sub-article (1) and paragraph (a), (b), (d) of sub-article (2) of Article 3 of this Regulation for natural and legal person, respectively.

5/ Application to transfer artisanal mining license by inheritance in accordance with Article 40 of the Proclamation shall be attached with the following:

a) certificate of heir and information specified under Article 8 of this Regulation;

b) evidence showing that the transferee heir committed himself to meet all terms and conditions of the license.

6/ The transfer of license shall be permitted only after the Licensing Authority verifies that the following documents shall be attached with the application:

a) if it is confirmed that the licensee has fulfilled all its obligations in accordance with the Proclamation, regulation, directives and on terms of his license agreement;

b) if the total area to be possessed by the transferee is not more than the maximum size of the area specified by directive;

c) in case of inheritance, if the transferee previously hold a license and the total license area exceed the maximum size of the area permitted for a single person only if he prefers the inheritance;

d) if the transferee agrees to comply with mining laws, terms and conditions of the license, and the work program of the licensee.

7/ Except by way of inheritance, any exploration license may be transferred, if the following particulars are fulfilled;

ሀ) ባለፈቃዱ ቢያንስ የመጀመሪያውን ዓመት የምርመራ ሥራ ያከናወነ፣ በፈቃድ ስምምነቱ የተመለከተውን ዝቅተኛ የሥራ ፕሮግራም እና የወጪ ግዴታ የተወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) ለማስተላለፍ የተጠየቀው ፈቃድ ከአንድ ዓመት በላይ ቆይታ ያለው ከሆነ ባለፈቃዱ ፈቃዱን እስከሚያስተላልፍበት ጊዜ ድረስ ያለውን የሥራ ፕሮግራም እና የወጪ ግዴታ የተወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ,

ይሆናል፡፡

a) if the licensee has been discharged the first year exploration and fulfilled his obligation regarding to the minimum work program and expenditure specified in his license agreement;

b) if the licensee has been operating for more than one year, he shall be expected to fulfill his minimum obligation in relation to work program and expenditure responsibilities until the time of transfer,

## ፳.ፈቃድን ስለማገድና ስለመሰረዝ

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፮ (፫) እና (፬) እንደተጠበቁ ሆነው ባለፈቃዱ የዚህን ደንብ አንቀጽ ፶ ወይም በአዋጁ አንቀጽ ፵፮ (፪) የተደነገጉትን ጥፋቶች ከፈጸመ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማንኛውንም ፈቃድ ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ ፴፬ (፭) መሰረት ሊሰረዝ ይችላል፡፡

## 20.Suspension and Revocation of the licenses

1/ Without prejudice to Article 46 (3) and (4) of the Proclamation, the Licensing Authority may suspend or revoke license where the licensee commit contravention stated under Article 50 of this Regulation or Article 46 (2) of the Proclamation.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article an artisanal mining license may be revoked pursuant to Article 34(5) of the Proclamation.

## ክፍል ሦስት
## ስለ ግኝት እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች

## PART THREE
## CERTIFICATE OF DISCOVERY AND CERTIFICATE OF COMPITENCE

## ፳፩.ለግኝት የምስክር ወረቀት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩/ ማንኛውም ማዕድን ወይም የማዕድን ምልክት ያገኘ ሰው በግኝቱ ቦታ ላይ እንደ ሁኔታው ምልክት በማኖር ከምችቱ ይገኝበታል ተብሎ የሚገመተውን ክልል፣ የቦታ ልዩ ስም እና የማዕድኑን ዓይነት በመጥቀስ ወዲያውኑ የግኝት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊያመለክት ይችላል፡፡

፪/ ማዕድን ወይም የማዕድን ምልክት ያገኘ ማንኛውም ሰው የማዕድኑን ይዘት የሚያሳይ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት፣ የማዕድን ናሙና ማስረጃ እና ማዕድኑ ከተገኘበት ወረዳ ማዕድንን በተመለከተ ሥልጣን ከተሰጠው ጽሕፈት ቤት የድጋፍ ደብዳቤ ከማመልከቻው ጋር ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

## 21. Application for a Certificate of Discovery

1/ Any pe on who discovers indications or existence of minerals may immediately apply to the Licensing Authority for a certificate by placing a marker, as appropriate, to the location of discovery and shall specify the region, specific area, and the type of the minerals.

2/ Any person, who discovers indications or existence of minerals, shall submit application of discovery to the Licensing Authority, with the application indicating the nature of the minerals, laboratory result, samples of the minerals and supporting letter from the wereda office responsible with respect to mines, at the place where the mineral discovered.

**፳፪. ግኝትን ስለማጣራትና ስለምስክር ወረቀት**

፩/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የግኝት ማመልከቻው እንደደረሰው፡

ሀ) የቀረበውን ማመልከቻ ይመዘግባል፡ የግኝት ማመልከቻ የቀረበበት ሥፍራ እና ማዕድኑ ቀደም ሲል ብቸኛ የሆነ መብት የሚያስገኝ ፈቃድ ያልተሰጠባቸው፡ ወይም የፈቃድ ማመልከቻ ያልቀረበባቸው፡ ወይም ሥፍራው ያልተያዘ ወይም ያልተከለከለ መሆኑን ያጣራል፡

ለ) አመልካቹ ምልክት ያደረገበትን ሥፍራ የጂኦግራፊክ ኮኦርዲኔት፡ ማዕድኑ በሥፍራው ላይ በተፈጥሮ የሚገኝ መሆኑን፡ የማዕድኑን ናሙና እንደ አስፈላጊነቱም የማዕድኑን ሁኔታ የሚያሳይ የፎቶግራፍ ማስረጃ በመውሰድ እንዲሁም የማዕድኑን ይዘት በላቦራቶሪ በማስመርመር አመልካች ካስታወቀው ማዕድን ጋር ተቀራራቢነት ያለው መሆኑን ያጣራል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ግኝቱን ካጣራና የግኝቱ ሥፍራና ማዕድኑ የፈቃድ ማመልከቻ ሊቀርብባቸው የሚችል መሆኑን ካረጋገጠ በአዋጁ አንቀጽ ፵፱ መሠረት ለ፲፰ ወራት ጸንቶ የሚቆይ የግኝት የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡

**፳፫. የግኝት የምስክር ወረቀት ባለይዞታ መብት እና ግዴታ**

፩/ የግኝት የምስክር ወረቀት ባለይዞታ የሆነ ሰው የምስክር ወረቀቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ፈቃድ እንዲሰጠው ካመለከተና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ ወይም ፮ መሠረት የሚጠየቁ መስፈርቶችን ካሟላ እንደ አግባቡ የምርመራ ወይም የማምረት ሥራ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

፪/ የግኝት የምስክር ወረቀት ባለይዞታ የሆነ ሰው የግኝት የምስክር ወረቀቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የተገኘውን ማዕድን በተመለከተ የምርመራ ወይም የማምረት ሥራ ፈቃድ የማግኘት መብቱን ማስተላለፍ ይችላል፡፡

**22. Verification of Discovery and Certification**

1/ The Licensing Authority, up on receiving application, shall:

a) register the application, verify the nature of the minerals submitted and the location of the markers placed by the discoverer, and shall confirm that the area and the mineral in question are not subject to an exclusive right or an application thereof, and the area has not been reserved or excluded;

b) investigate and compare the similarity of the sample with the discovery sample submitted by taking the geographic coordinate where marker is placed, that the mineral naturally exists, the nature of the minerals, as the case may be, by taking photograph information.

2/ Where the discovery is verified in accordance with sub-article (1) of this Article, the area and the mineral is subject to license application, the Licensing Authority shall, pursuant to Article 49 of the Proclamation, issue a discovery certificate to the discoverer valid for 18 months from its date of issuance.

**23. Rights and Obligations of a Holder of Certificate of Discovery**

1/ A holder of certificate of discovery shall have the right to be granted exploration or mining license during the term of validity of such certificate; if lodges application for such license if he meets the necessary requirements provided under Article 4 or 6 of this Regulation.

2/ A holder of certificate of discovery, during the term of validity of the discovery certificate, may transfer his right to an exploration or mining licensee to the minerals he has discovered.

**፳፬. የማማከር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ**

በማዕድን ዘርፍ የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፦

፩/ አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፦

ሀ) ሙሉ ስሙን፣ ፆታውን፣ ዜግነቱን፣ የትውልድ ቦታውን እና የመታወቂያውን ቅጂ፣

ለ) ሙያውን፣

ሐ) የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻውን፣

መ) የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተጠየቀበት የሙያ ዘርፍ፣

ሠ) የትምህርት ብቃት ማስረጃ ቅጂ እና በመመሪያ በሚገለፀው መሰረት አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ማስረጃ ቅጂ፣

ረ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መረጃዎች፡፡

፪/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ፡

ሀ) ስሙን፣ ዜግነቱን፣ የሕግ አቋሙን፣

ለ) የዋና መሥሪያ ቤቱን አድራሻ፣

ሐ) የተቀጣሪ ባለሙያዎች የትምህርት፣ የሥራ ውል እና በመመሪያ በሚገለፀው መሰረት አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ማስረጃ፣

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (መ) እና (ረ) የተጠቀሱት መረጃዎች፣

ሠ) ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመሥረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂ፣

ረ) በአመልካቹ ድርጅት ስም ለመፈረም ሥልጣን የተሰጠውን ኃላፊ ስምና ማንነት የሚገልጽ ማስረጃ፡፡

**፳፭. የማማከር አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፬ መሠረት ተሟልቶ የቀረበ ማመልከቻ ተገቢው የማመልከቻ ክፍያ እንደተፈጸመ ይመዘገባል::

**24. An application for a certificate of professional competence for consultancy**

An application for certificate of professional competence for consultancy shall be attached with the following information;

1/ If an applicant is a natural person:

a) his full name, sex, nationality, place of birth and copy of identification card;

b) profession;

c) his residential address;

d) discipline for which certificate of professional competence for consultancy service is requested;

e) the copies of necessary educational qualification document and work experience as specified in the directive to be issued;

f) other information determined in the directive of the Licensing Authority.

2/ If the applicant is a legal person:

a) its name, nationality, legal form;

b) address of its head office;

c) employee profiles such as education, work experience and employment contract as specified in the directive;

d) information specified under paragraph (d) and (f) of sub-article (1) of this Article;

e) authenticated copy of memorandum and articles of association;

f) the name of an official authorized to sign on behalf of the applicant business organization.

**25. Issuance of a Certificate of Professional Competence for Consultancy Service**

1/ An application that meets the requirements provided under Article 24 of this Regulation shall be registered upon the payment of the prescribed application fee.

፪/ ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው የቀረቡ ሰነዶች በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት አግባብ ያላቸው ስለመሆኑ ይጣራል፣ ይገመገማል::

፫/ የአመልካቹ ጥያቄ ተቀባይነት ሲያገኝ በቅኝት፣ በምርመራ፣ በቅድመ-አዋጭነትጥናት፣ ፀአዋጭነት ጥናት፣ በማምረት እና በሌሎች የማዕድን ሥራ ዘርፎች የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

**፳፮.የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ፣ ዕድሳትና ስለመሰረዝ**

፩/ የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለአንድ ዓመት ፀንቶ ይቆያል፡፡

፪/ የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው አንድ ዓመቱ ከመጠናቀቁ ከ፴ (ሰላሳ) ቀናት በፊት ተገቢውን የዕድሳት ክፍያ በመፈጸም የምስክር ወረቀቱ እንዲታደስለት በጽሁፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፫/ የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚታደሰው በየዓመቱ ይሆናል፡፡

፬/ የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ባለቤት የማዕድን ኢንዱስትሪው የሚጠይቀውን ወቅታዊ የሙያ ብቃትና ቴክኖሎጂ ያገናዘበ እንዲሁም ሙያዊ ሥነ-ምግባርን ያሟላ አገልግሎት መስጠት አለመቻሉ በሚኒስቴሩ ከተረጋገጠ የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን ከማለቁ በፊት ሊሰረዝ ይችላል፡፡

፭/ የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ባለቤት በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሠረት የሙያው ሥነ-ምግባርና የቴክኒክ ብቃቱ የሚጠይቀውን ግዴታ ያልተወጣ መሆኑ ከተረጋገጠ የምስክር ወረቀቱ አይታደስም፡፡

፮/ ሚኒስቴሩ የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበትን ወይም ዕድሳት የተከለከለበትን ምክንያት ለምስክር ወረቀቱ ባለቤት በ ፲ (አስር) ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፯/ የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ሰው ለስረዛው ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች ካስተካከለ ከአንድ ዓመት በኋላ አዲስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል ፡፡

2/ The eligibility of the attached documents to the application shall be assessed and verified in accordance with the directives to be issued.

3/ Where the Licensing Authority finds the application acceptable, it shall grant a certificate of professional competence in the area of reconnaissance, an exploration, pre-feasibility and feasibility studies, mining as well as for other mining operations.

**26. Duration, Renewal and Revocation of a Certificate of Competence for Consultancy**

1/ A certificate of competence for consultancy services shall be valid for the period of one year.

2/ The holder of a certificate of competence for consultancy services shall, 30 days prior to the expiry date, have the right to apply in writing for a renewal by effecting payment of prescribed application fee.

3/ The certificate of competence for consultancy services shall be renewed annually.

4/ Where the Ministry proves that the holder of a certificate of competence for consultancy service failed to carry out his duties in an ethical manner and to use modern technology and good mining operation practice generally accepted in the mining industry, the Licensing Authority may revoke the certificate prior to the expiry of the validity period.

5/ The certificate of competence for consultancy services shall not be renewed, if the Licensing Authority proves that the applicant has failed to comply with professional ethics and technical obligations in accordance with the terms of his certificate of competence.

6/ The Ministry shall notify, in writing, to the applicant his decision of rejection for renewal, or reasons for revocation of the existing certificate of competence for consultancy services within 10 days.

7/ The applicant may apply for issuance of a new certificate of competence for consultancy services after one year from the time he has rectified the causes for revocation.

፰/ የዕድሳት ጊዜን ባለማክበር የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ሰው ከተሰረዘበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት ሌላ ፈቃድ ማግኘት አይችልም፡፡

፱/ የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዕድሳት የተከለከለ ሰው ዕድሳቱን ያስከለከሉ ምክንያቶችን ካስተካከለ ከአንድ ዓመት በኋላ አዲስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## ፳፯.የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

በማዕድን ዘርፍ የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፦

፩/ አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፦

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፬ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) የተዘረዘሩትን፣

ለ) የትምህርት ማስረጃ ቅጂ፣

ሐ) በሙያው ቀደም ሲል ያገለገለ ከሆነ የሥራ ልምድ ማስረጃ፣

መ) ለሚሰማራበት የቴክኒክ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ የቁሳቁስ ዝግጅትን የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ፡፡

፪/ አመልካች በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ከሆነ፦

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፬ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተዘረዘሩ መረጃዎችን፣

ለ) ድርጅቱን በኃላፊነት እንዲመራ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ስሙን፣ ዜግነቱንና የመኖሪያ አድራሻውን፣

ሐ) በድርጅቱ ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞችን አግባብ ያለው የትምህርት፣ የሥራ ልምድ እና ከሠራተኞቹ ጋር የተዋዋለበትን የሥራ ውል ማስረጃ፣

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (መ) የተጠቀሱትን ማስረጃዎች፣

ሠ) በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበትን የመመሥረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጅ፡፡

8/ A person, whose certificate of competence for consultancy services is revoked due to non observance of renewal period, may not be granted another certificate for one year starting from the date of revocation of the previous certificate.

9/ The applicant, pursuant to the directives to be issued by the Licensing Authority, may apply for a renewal of a certificate of competence for consultancy services after rectifying the causes that led the reject his application for renewal.

## 27.Application for a Certificate of Competence for Technical Service.

An application for certificate of competency for technical service in mining sector shall contain the following:

1/ where the applicant is anatural person:

a) information specified under paragraph (a), (b) and (c) of Article 24 (1) of this Regulation;

b) copy of educational qualification;

c) documents of previous work experience, if any;

d) documents showing the material preparation of the applicant for intended technical service.

2/ where the applicant is a legal person:

a) information specified under paragraph (a) and (b) of Article 24(2) of this Regulation;

b) name, address and nationality of the person who authorized to sign on behalf of the applicant organization;

c) relevant documents of educational back ground, work experience and employment contract made with the employee;

d) documents specified under paragraph (d) of sub-article (1) of this Article;

e) original and a copy of memorandum and articles of association authenticated by relevant authority.

**፳፰. የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት፣ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣ ስለ እድሳትና ስለመሠረዝ**

፩/ የማዕድን ዘርፍ የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፯ መሠረት ተሟልቶ ሲቀርብ ተገቢው ክፍያ መፈጸሙ ተረጋግጦ ይመዘገባል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አመልካች ያቀረበው ማመልከቻ ለምስክር ወረቀት አሰጣጥ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ማሟላቱን ሚኒስቴሩ መርምሮ ካረጋገጠ በኋላ የምስክር ወረቀቱን ይሰጠዋል፡፡

፫/ የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለአንድ ዓመት ፀንቶ ይቆያል፡፡

፬/ የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ የሚቆይበት ዓመት ከመጠናቀቁ ከ ፴ ቀናት በፊት የምስክር ወረቀቱ እንዲታደስለት በጽሑፍ መጠየቅ ይችላል፡፡

፭/ ሚኒስቴሩ ተገቢው የእድሳት ክፍያ መፈጸሙን፣ አዋጁን፣ ደንቡንና መመሪያዎችን የሚጥስ ተግባር አለመፈጸሙን ካረጋገጠ የምስክር ወረቀቱን ሊያድሰው ይችላል፡፡

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፭) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ሚኒስቴሩ በሚከተሉት ምክንያቶች በማንኛውም ጊዜ የምስክር ወረቀቱን ሊሰርዘው ይችላል፦

ሀ) የአገልግሎት አሰጣጡ በመመሪያ ከሚወሰነው ደረጃ በታች ሲሆን፣ እና

ለ) የአዋጁን፣ የደንቡንና መመሪያዎችን ድንጋጌ የሚጥስ ተግባር ሲፈጸም፡፡

፯/ ሚኒስቴሩ የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከሰረዘ ወይም ዕድሳት ከከለከለ ምክንያቶቹን በመዘርዘር በ ፲ (አስር) ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፰/ የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ሰው ለስረዛው ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች ካስተካከለ ከአንድ ዓመት በኋላ አዲስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ጠይቆ ማግኘት ይችላል፡

**28. Issuance, Duration, Renewal and Revocation of Certificate of competence for technical service**

1/ Application to obtain certificate of competence for technical service in mining sector if submitted according to Article 27 of this Regulation by fulfilling the requirements, it shall be registered by ascertaining payment of appropriate fees.

2/ The Ministry shall issue a certificate to the applicant, upon verifying that the application lodged pursuant to sub-article (1) of this Article fulfills the conditions specified for the issuance of a certificate.

3/ A certificate of competence for technical service shall be valid for one year.

4/ The holder of certificate of competence for technical service may apply in writing for renewal 30 days prior to the expiry of the validity period.

5/ The Ministry may renew a certificate after verifying the payment of renewal fees, provided that the applicant has not contravened any provision of the Proclamation, Regulations and directives.

6/ Notwithstanding the provision of sub-article (3) and (5) of this Article, the Ministry may at any time revoke the certificate competence on the following grounds:

a) where the service delivery is below the standard required by directive;

b) where there is a breach of any provision of the Proclamation, Regulations and directives.

7/ Where the Ministry revokes or refuses renewal a certificate of competence, it shall notify the applicant in writing the reason in detail within 10 days.

8/ The holder whose certificate of competence revoked may apply for issuance of a new certificate of competence after one year counted from the date of revocation by rectifying the causes of revocation.

፱/ የእድሳት ጊዜን ባለማክበር የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ባለፈቃድ የምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት ሌላ ፈቃድ ማግኘት አይችልም፡፡

## ክፍል አራት
## የባለፈቃዶች መብቶችና ግዴታዎች

### ምዕራፍ አንድ
### መብቶች

**፳፱+ስለ መሠረተ ልማት አውታሮችና ስለ ሌሎች ግንባታዎች**

፩/ ባለፈቃዱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ ልማት አውታሮችና ሌሎች ግንባታዎችን መገንባት ይችላል፡፡

፪/ በባለፈቃዱ የሚሠሩ የመሠረተ ልማት አውታሮች ተገቢ የሆነ ዲዛይንና የቴክኒክ አሠራር መከተልና አግባብ ባለው መመሪያ መሠረት ደህንነቱ የተጠበቀና ቀልጣፋ አገልግሎት ሊሰጡ በሚችሉበት አኳኋን መገንባት፣ መጠገንና ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡

፫/ ባለፈቃዱ የሠራቸው የመሠረተ ልማት አውታሮች ከሕዝብ አገልግሎት ውጪ ለሆነ ማናቸውም የንግድ ዓላማ አገልግሎት እንዲውሉ የሚደረግ ከሆነ የመሠረተ ልማት አውታሮቹን ለመገንባትና ጥገና ለማካሄድ የወጣው ወጭ ለንግድ ዓላማ በሚጠቀሙ ተጠቃሚዎች መካከል እንዲከፋፈል ባለፈቃዱ ፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ጥያቄ ሲቀርብ፡

ሀ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የእያንዳንዱን ተጠቃሚ የተጠቃሚነት ድርሻ መሠረት በማድረግ ወጭውን ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ያከፋፍላል፣

ለ) በተጠቃሚዎች መካከል የሚከፋፈለው ወጭ የመሠረተ ልማት አውታሮቹ ዓመታዊ የእርጅና ቅናሽ፣ የሥራ ማስኬጃና የጥገና ወጭዎች ጠቅላላ ድምር ይሆናል፣

ሐ) ዓመታዊ የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው ተቀናሽ ያልሆነውን የመሠረተ ልማት አውታሮቹ የካፒታል ወጭ ለባለፈቃዱ ቀሪ የፈቃድ ዘመን ዓመታት በማካፈል ይሆናል፡፡

9/ The holder of a certificate whose certificate is revoked due to non-observance of renewal period may not be granted another certificate for one year starting from the date of revocation of previous certificate.

## PART FIVE
## RIGHTS AND OBLIGATIONS OF THE LICENSEES

### CHAPTER ONE
### RIGHTS

**29. Infrastructure and other constructions**

1/ The licensee may erect infrastructure and other constructions which are necessary for the mining operation.

2/ Infrastructures and other facilities to be built by the licensee shall conform to appropriate designs and technical standards and be constructed, maintained and operated, as per the directives, in a manner to assure their safety and efficient use.

3/ If the infrastructure constructed by licensee is to be used for any commercial purposes, other than public services, the licensee may request the Licensing Authority to allocate the cost of the construction and operation of such infrastructure among such commercial purpose users.

4/ When request is submitted by licensee pursuant to sub-article (3) of this Article:

a) the Licensing Authority shall allocate the cost on the equitable basis taking into account the extent of the use thereof;

b) the cost to be allocated by the Licensing Authority among the users shall be the total annual depreciation and the costs of operation and maintenance of such facilities;

c) the annual depreciation shall be computed by dividing the amount of un-depreciated capital cost of such infrastructure by the numbers of years remaining for the term of the licensee's license.

፭/ ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃድ ክልሉ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን ለመዘርጋት በፈቃድ ክልሉና በአዋሳኝ ከሚገኝ ቦታ ብቸኛ የሆነ መብት ቀድሞ የተሰጠበት እስካልሆነ ድረስ ለግንባታው በሚያስፈልገው መጠን ብቻ የግንባታ ማዕድን መጠቀም ይችላል፡፡ ከፈቃድ ክልሉ ወጪ ለሚጠቀማቸው የግንባታ ማዕድናት በቅድሚያ የሚመለከተውን አካል ማስፈቀድ አለበት፡፡

፴. በቅኝት ወይም በምርመራ ወቅት በተገኙ ማዕድናት ላይ ስለማዘዝ

፩/ የምርመራ ወይም የቅኝት ባለፈቃድ ያገኛቸውን በፈቃዱ ላይ የተጠቀሱትንም ሆነ ሌላ ማዕድን ይዞ ለመቆየት ወይም ሊያዝበት የሚችለው ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በማመልከት ሲፈቀድለት ይሆናል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን እንደአግባቡ ማዕድኑን ከፈቃዱ ቦታ እንዲነሳና አመልካቹ ገቢ ግብር እና ሮያልቲ ከፍሎ ይዞ እንዲቆይ ወይም እንዲያዝበት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በቅኝት ወይም በምርመራ ወቅት የተገኘ ማዕድን ባለፈቃዱ ይዞ እንዲቆይ ወይም እንዲያዝበት ለማድረግ የማይፈቀድለት ሆኖ ከተገኘ ማዕድኑ የመንግሥት ንብረት ሆኖ ይቆያል፡፡

፴፩. ስለአየር ላይ ፎቶግራፎች፣ ምስሎችና ሌሎች መረጃዎች

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ በቅድሚያ ከፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሚያገኘው መረጃና ድጋፍ መሠረት የሚመለከተውን መንግሥታዊ አካል በማስፈቀድ ከአየር ላይ ፎቶግራፎችንና ምስሎችን ማንሳት፣ የጂኦፊዚክስና ሌሎች ከአየር ላይ የሚወሰዱ መረጃዎችን መሰብሰብ ይችላል፡፡

፪/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ያነሳቸውን የአየር ላይ ፎቶግራፎችና ምስሎች እንዲሁም የጂኦፊዚክስ እና ሌሎች ከአየር ላይ የተወሰዱ ጥሬ መረጃዎች ቅጂ ወዲያውኑ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን መስጠት አለበት፡፡

5/ Any licensee may use construction minerals from the license area and an area adjacent to the license area only to the extent required for the construction, unless a third party had been granted with an exclusive right over the area prior to the issuance of the license. Where the construction mineral is out of the license area, the licensee shall obtain authorization from appropriate organ.

30. **Disposal of Minerals Obtained during Exploration and Reconnaissance**

1/ The holder of an exploration and reconnaissance license shall apply to the Licensing Authority and obtain permission to retain or dispose of any minerals he discovers, whether mentioned in the license or not.

2/ The Licensing Authority, as appropriate, may authorize the removal of minerals from the license area, or he may authorize the applicant to retain and dispose of the minerals with the payment of prescribed income tax and royalty.

3/ Without prejudice to sub-article (2) of this Article, if the mineral discovered during reconnaissance or exploration period is not permitted for retention or disposal, it shall remain to be property of Government.

31. **Aerial photographs, Images and other information**

1/ Any licensee may take aerial photographs, images, geophysics and other aerial data by the permission of concerned Government Office based on the prior information and support of the Licensing Authority.

2/ The licensee shall promptly submit to the Licensing Authority copies of all aerial photographs as well as geophysics and other row aerial data taken pursuant to sub-article (1) of this Article.

፫/ ማንኛውም ሰው በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ዘንድ የሚገኙ ሚስጥር ያልሆኑ ካርታዎችንና መረጃዎችን የማየት መብት ይኖረዋል፡፡

**፴፪.** <u>ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ስለመሆን</u>

፩/ የማዕድን ምርመራ ሥራ ባለፈቃድ ለማዕድን ሥራው አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ የሚያስፈልግ ስድስት ሰው የሚይዝ አነስተኛ አውሮፕላን ወይም ሄሊኮፕተርን ጨምሮ ሌሎች ለሥራው አግባብነት ያላቸውን የመመርመሪያ መሳሪያዎች ፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን በመጠየቅ ሲፈቀድለት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ የማዕድን ምርመራ ሥራ ባለፈቃድ በፈቃድ ክልሉ በረራ በማድረግ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግል አውሮፕላን ወይም ሄሊኮፕተር ለማብረር ከሚመለከተው የሲቪል አቪዬሽን መስሪያ ቤት ፈቃድ እንዲያገኝ ድጋፍ መስጠትን ያካትታል፡፡

፫/ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብቱን ለመጠቀም ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውም ባለፈቃድ ጥያቄውን በሚያቀርብበት ወቅት የሚፈለግበትን የማዕድን ሀብት ልማት ሥራና ዝቅተኛ የወጪ ግዴታ መወጣቱን የሚያረጋግጥ ሰነድ ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

፬/ በአዋጁ አንቀጽ ፸፭ መሠረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ መብት አጠቃቀምን በተመለከተ ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

፭/ በአዋጁ አንቀጽ ፸፭(፯) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የማዕድን ሥራ ፈቃድ ሲቋረጥ ወይም ባለፈቃዱ የፈቃድ መብቱን ሲተው ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ የገቡ ዕቃዎችን አግባብ ባለው የጉምሩክ ሕግ መሠረት ተገቢውን የጉምሩክ ፎርማሊቲ ፈጽሞ ሊሸጥ ወይም ለሌላ ተመሳሳይ መብት ላለው ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፮/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ ፸፭ (፫) መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት ከምርት ሥራ ፕሮግራሙ ጋር የተጣጣመ ፍላጎቱን በቅድሚያ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በማቅረብ ማስፀደቅ ይኖርበታል፡፡

3/ Any person shall have access to all available non-confidential maps and data which is found within the Office of Licensing Authority.

**32. <u>Exemption from Customs Duties and Taxes</u>**

1/ Up on the request of the holder of exploration license, the Licensing Authority may grant permission to the licensee so as to import small aircraft or helicopter having seat of 6 persons to be used for collecting data and other machineries required for its operation free of customs duties and taxes.

2/ The permission granted pursuant to sub-article (1) of this Article may include provision of support letter to the exploration license holder to get permission from civil aviation authority to fly aircraft required over the license area to collect data.

3/ Any licensee who applies to exercise his right for exemption from customs duties and taxes shall attach with his application a document that verifies he has discharged general obligations of mining operation and minimum work expenditure.

4/ The Ministry shall issue detail directive on exemption of customs duties and taxes as specified under Article 75 of the Proclamation.

5/ Without prejudice to Article 75(7) of the Proclamation, when any mining operation license is terminated or the licensee surrenders his license, any item imported free of custom duties and taxes, may sell upon fulfilling customs formalities or transfer to another person having similar right in accordance with appropriate laws.

6/ The holder of small scale and large scale mining license, pursuant to Article 75 (3) of the Proclamation, in order to import free of custom duties and taxes, shall obtain prior approval from the Licensing Authority by submitting request of items corresponding to the approved work program.

፯/ ከባህላዊ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም አሸዋ ወይም ገረጋንቲ ለማምረት ከሚያስችል የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በስተቀር ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተፈቀዱለትን መሳሪያዎች፣ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች በማዕድን ማምረት ቅድመ-ዝግጅት ጊዜ ማስገባት ካልቻለ ማዕድን ማምረት ከጀመረ በኋላ እስከ አምስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት ይችላል፡፡

፰/ በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም ያልተካተተ ማንኛውንም ቋሚ ዕቃ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት የሚቀርብ ጥያቄ የሥራ ፕሮግራም ማስተካከያ ማመልከቻ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ቀርቦ ሲፈቀድ ብቻ ይስተናገዳል፡፡

፱/ የፈቃድ ዘመኑ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሊጠናቀቅ ዘጠኝ ወራት ሲቀረው በማዕድን ምርመራ ሥራ ባለፈቃድ የሚቀርብ ማናቸውም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

**፴፫.** **<u>ስለማዕድናት ናሙና</u>**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የማዕድን ሥራ ባለፈቃድ በሀገር ውስጥ ለማስመርመር አለመቻሉን በማረጋገጥ፣ ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን በማስፈቀድ እና ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈፀም እንደአግባቡ በፈቃዱ የተመለከቱትን የማዕድን ናሙናዎች ለላቦራቶሪ ምርመራ ወይም ለገበያ ጥናት ወደ ውጪ አገር መላክ ይችላል፡፡

፪/ አግባብ ያለው የከበሩ ማዕድናት ግብይት ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ሰው በሀገር ውስጥ ለማስመርመር አለመቻሉን በማረጋገጥ፣ ፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን በማስፈቀድ እና የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም የማዕድን ናሙናዎችን ለላቦራቶሪ ምርመራ ወይም ለገበያ ጥናት ወደ ውጪ አገር መላክ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት የማዕድን ናሙናዎችን ወደ ውጪ አገር ለመላክ የሚጠይቅ አመልካች እንደ አግባቡ የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡

7/ The holder of any mining license, except artisanal mining licensee or construction minerals mining licensee issued for the mining of sand or selected materials, may import consumables which are approved for mining development period in accordance with sub-article (3) of this Article free of customs duties and taxes within five year from the date he starts mining production, where he fail to import them during the time of preparation of mining operation.

8/ Any application for exemption of non-consumable goods from customs duties and taxes, that were not included in the approved work program, shall only be accepted if the application for the amendment of the applicable work program submitted and the Licensing Authority approves thereof.

9/ No application regarding exemption from customs duties and taxes shall be accepted, if the exploration licensee remains with nine months of validity period to expire his license.

**33. <u>Samples of minerals</u>**

1/ Without prejudice to Article 44 of the Proclamation, any licensee, by the permission of the Licensing Authority and upon payment of prescribed fees, may export samples of minerals which are stated in license and for which local laboratory test is not possible, as appropriate, to conduct laboratory testing or for the purpose of market analysis.

2/ Without prejudice to relevant laws regarding Transaction of Precious Minerals, any person may export samples of minerals to conduct testing or for the purpose of market analysis, where local laboratory test is not possible and by the permission of the Licensing Authority and upon payment of prescribed fees,.

3/ An applicant who requested to export sample of minerals pursuant to sub-article (1) and (2) of this Article, shall present the following information, as appropriate:

ሀ) የአመልካቹን ሙሉ ስም፣ ፊርማና እንደአግባቡ ማህተም ያለበት የናሙናውን ዓይነት፣ መጠን፣ የሚላክበትን ዓላማና አገር የሚገልጽ ማመልከቻ፣

ለ) አመልካቹ በምርምር ተቋማት የሚሠራ ወይም በውጪ አገር ከፍተኛ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኝ ሰው ከሆነ ናሙናዎቹ ለትምህርታዊ ምርምር አስፈላጊ መሆናቸውን የሚገልጽ አግባብ ካለው ተቋም የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ ዋና ቅጂ፣

ሐ) አመልካቹ የንግድ ድርጅት ከሆነ አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ፣

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ከተደነገገው ውጪ የሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው የማዕድን ናሙናዎችን ወደ ውጪ አገር ለመላክ የፈለገበትን ምክንያት እና እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ በመመሪያ ያስፈልጋሉ ብሎ የወሰናቸውን ሌሎች መረጃዎች፣

ሠ) የንግድ ጥቅም የሌለው ስለመሆኑ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን መረጋገጡ እንደተጠበቀ ሆኖ ለተፈለገው ዓላማ የሚሆን መጠን ያለው ማዕድን ናሙና፡፡

፬/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የማዕድን ናሙናዎች ሲቀርቡለት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ለሚመለከተው የጉምሩክ መስሪያ ቤት የይለፍ ደብዳቤ በመፃፍ ከሀገር እንዲወጡ ሊፈቅድ ይችላል፣

ሀ) በቀረቡት የማዕድን ናሙናዎች ላይ ፊዚካላዊ ምርመራ በማካሄድ ናሙናዎቹ በማመልከቻው የተጠየቁት መሆናቸው ሲረጋገጥ፣

ለ) ናሙናው በማመልከቻ ከተጠየቀው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ያረጋገጠው ባለሙያ ወይም ኃላፊ ፊርማና የመስሪያ ቤቱ ማህተም ተደርጎበት በቀረበለት መያዣ ዕቃ ውስጥ ተደርጎ ሲታሸግ፣

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለላቦራቶሪ ምርመራ ከአገር እንዲወጣ የሚፈቀድ የማዕድን ናሙና እና መጠን በመመሪያ ይወሰናል፡፡

a) full name, signature of the applicant and, as the case may be, an application with stamp that describes the type, quantity, purpose of the export and the country where samples to be exported;

b) original copy of recommendation letter from appropriate organization that confirms samples to be exported are necessary for research, if the applicant is an employee of the research institute or a student of higher education abroad;

c) investment license and valid business license from appropriate government body, if the applicant is a business organization;

d) any other person other than those specified under paragraph (b) and (c) of this sub-article who applies to export samples to abroad, shall provide the reasons for the export, and as the case may be any other necessary information as determined in the directive of the Ministry;

e) subject to the approval of its non-commercial purpose by the Licensing Authority, quantity of samples to be used for the test.

4/ When sample mineral are presented pursuant to sub-article (3) of this Article, the Licensing Authority may permit export of the sample by issuing pass letter to the concerned customs authority upon verifying fulfillment of the following conditions:

a) verifying that the sample is the same with the one proposed in the application by conducting physical examination on the sample;

b) where an expert or a head approved the conformity of the samples and sealed it with the submitted container and thereby put his signature and affixed it with a stamp.

5/ The sample and the quantity that may be exported for laboratory testing pursuant to this Article shall be determined by directive.

፮/ የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ ለምርመራ ሥራ ከሚከናወን የጂኦኬሚስትሪ እና የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ የሰበሰባቸውን የኮር ናሙናዎች ዝርዝር ማስቀመጥና ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማስረከብ ይኖርበታል፡፡

፯/ በክልል የተሰጠ ፈቃድ ያላቸው ባለፈቃዶች ናሙና ለመላክ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ ፈቃዱን ከሰጣቸው ክልል የድጋፍ ደብዳቤ ሲያቀርቡ ብቻ ይስተናገዳሉ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ግዴታዎች

### ፴፬. ወሰን ስለመከለል

፩/ ማንኛውም ለአነስተኛ ወይም ለከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ወይም እንዲሰጠው ማመልከቻ ያቀረበ ሰው ፈቃድ የጠየቀበትን ሥፍራ በእያንዳንዱ የወሰኑ መታጠፊያና የቀጥታ መስመር ክፍልፋይ ላይ ምልክት በማድረግ መከለል አለበት፡፡

፪/ በወሰኑ መታጠፊያዎች እና በወሰኑ ቀጥታ መስመር የሚደረጉ ምልክቶች እያንዳንዳቸው እንደ ቅደም ተከተላቸው ዲያሜትራቸው ከ፳፭ ሴንቲ ሜትር እና ፲ ሴንቲ ሜትር የማያንሱ የተጠረቡ ድንጋዮች፣ ብረቶች ወይም የመሳሰሉ ቁሶች ሆነው ከፍታቸው ከመሬት ቢያንስ አንድ ሜትር ሆኖ መሬት ላይ በደንብ መቸከል አለባቸው፡፡

፫/ በወሰን መታጠፊያ እና በወሰን ቀጥታ መስመር በሚደረግ በእያንዳንዱ ምልክት ላይ የአመልካቹ ስምና የፈቃድ ቁጥሩን የሚገልፅ ምልክት መለጠፍ አለበት፡፡

፬/ ባለፈቃዱ የፈቃድ ክልሉ ወሰን በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ መሠረት የሚደረጉ ለውጦችን እንዲያንጸባርቅ አድርጎ መከለልና ምልክቶቹ ለውጡን እንዲያሳዩ አድርጎ ማስተካከል አለበት፡፡

፭/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የፈቃድ ማመልከቻ የቀረበበትን ወይም ፈቃድ የተሰጠበትን ሥፍራ ወሰን አከላለል በባለሙያ እንዲመረመርና ወሰኑም እንዲረጋገጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

6/ The holder of exploration license shall retain and submit to the Licensing Authority duplicate of core samples which are collected from geo-chemistry and boreholes of his exploration work.

7/ The request to export samples by the holders of the license issued by Regional Governments shall only be accepted if the holders present recommendation letter from concerned regional authorities.

## CHAPTER TWO

## OBLIGATIONS

### 34. Delimitation of Boundaries

1/ Any person who is the holder or applicant of small scale or large scale mining license shall, delimit the area for which the application is to be submitted by placing markers at each turning point along the boundary of the area and along each straight segment.

2/ The markers placed at each turning point and segment along a boundary shall be of masonry, metal or such other similar materials having not less than 25 and 10 cm diameters respectively; and shall have height at least be one meter above the ground and tightly be fixed on the ground.

3/ The sign indicating the name of the applicant and the registration number of the licensee shall be fixed at each markers placed at each turning point and segment along a boundary.

4/ A licensee shall also adjust the delimited boundary of his license area to reflect any change therein, pursuant to Article 22 of the Proclamation and shall reposition all markers to reveal accurately such change.

5/ The Licensing Authority may cause expert examination and verify the delimitation of boundaries of license area for which application is submitted or already license is issued.

፮/ የተከለለው ወሰን በቀረበው ማመልከቻ ወይም በፈቃዱ ላይ የተገለጸውን ሥፍራ በትክክል የማያሳይ መሆኑን ባለሙያ ያረጋገጠ እንደሆነ ወሰኑ በዚሁ መሠረት መስተካከል እና ለቀየሳው የወጣው ወጪ በአመልካቹ ወይም በባለፈቃዱ መሸፈን አለበት፡፡

## ፴፭.ስለ ምርመራ ሥራ ፕሮግራምና ስለወጭዎች

፩/ የምርመራ ፈቃድ ለማግኘት ያመለከተ ሰው የሚያቀርበው የሥራ ፕሮግራምና የወጭ ዝርዝር ማመልከቻ የቀረበበትን ሥፍራ፣ የማዕድኑን ዓይነት፣ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽእኖ ግምገማ ጥናትና የማህበረሰብ ልማት፣ ሊያከናውን የሚችለውን የማዕድን ሥራ ባህርይ በማገናዘብ ተገቢ ከሚሆነው የሥራ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነና በመመሪያ የሚወሰነውን ዝቅተኛ የሥራ ፕሮግራምና የወጪ ግዴታ የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

፪/ የቀረበው የሥራ ፕሮግራምና የወጪ ዝርዝር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጹትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቀረበውን ፕሮፖዛል ያፀድቀዋል፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የቀረበው የሥራ ፕሮግራምና የወጪ ዝርዝር በቂ ሆኖ ካላገኘው ምክንያቶችን በመግለጽ አመልካቹ የሥራ ፕሮግራሙንና የወጭ ዝርዝሩን እንዲያስተካክል በጽሑፍ ያሳውቀዋል፡፡

፬ ባለፈቃዱ በማንኛውም ዓመት ሊያከናውን ግዴታ ከገባው ሥራ በላይ ካከናወነ እና ወጭ ካወጣ ከግዴታው በላይ የፈጸመው ሥራ ወይም ያወጣው ወጪ ከተሠራው ሥራ ጋር ተገናዝቦ አግባብነት ሲኖረው ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተቀባይነት ያገኘውን ዝቅተኛ የሥራ ፕሮግራም ሳያሟላ እና በቅድሚያ የፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን ስምምነት ሳያገኝ ከዝቅተኛ ወጪ በላይ ያወጣ ባለፈቃድ ወጪው እንደ ማዕድን ሥራ ወጪ ሊያዝለት አይችልም፡፡

፮/ ማንኛውም የምርመራ ባለፈቃድ በሁለተኛውና በሶስተኛው ዓመት ሊሠራ ያሰበውን ዝርዝር የሥራ ፕሮግራምና ዝቅተኛ የወጪ መጠን እንዲሁም የተሟላ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽእኖ

6/ If the expert verifies that the boundaries do not accurately reflect the area requested in an application or specified in the license, such boundaries shall be adjusted accordingly, and the applicant or licensee, shall born the cost of adjustment.

## 35. Work programs and Expenditure for an exploration

1/ The work program and expenditure proposed by the applicant for an exploration license shall correspond to an appropriate level of mining operations, taking into account the area for which the application is submitted, the type of minerals, environmental and social impact assessment and community development plan, and meet minimum work and expenditure requirements as specified by directive.

2/ Where the proposed work program and expenditure meet the requirements specified under sub-article (1) of this Article the Licensing Authority shall approve the proposal.

3/ Where the Licensing Authority finds that the proposed work program and expenditure are inadequate, it shall state the comments and notify the applicant in writing to rectify the work program.

4/ Where the licensee performs work in access and incurs expenditure in any year, the work he performed and expenditure incurred in excess of his obligation may be accepted by taking in to account their appropriateness.

5/ Where the licensee incurs expenditure in excess, without fulfilling the minimum requirements as provided under sub-article (1) of this Article and without getting prior approval from Licensing Authority, such expenditure shall not be considered as expenditure of the mining operation.

6/ Any holder of an exploration license shall submit and get approval from the Licensing Authority for the minimum work program and expenditure of the second and third

ግምገማ ጥናት ሪፖርት የመጀመሪያ ፈቃድ ዓመት ከማለቁ ከ፴ (ሰላሳ) ቀናት በፊት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብና ማስጸደቅ አለበት፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ መሠረት ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የምርመራ ሥራ ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ ያልቻለበትን ወይም በላቀ ሁኔታ ለማከናወን የፈለገበትን ሁኔታዎች በማስረዳት የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከትና ማስጸደቅ አለበት፡፡

## ፴፮.ስለልማት፣ የምርት ፕሮግራም እና ስለወጪዎች

፩/ የአነስተኛ፣ የከፍተኛ ወይም እንደ ሁኔታው የልዩ አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ለልማትና ለምርት ፕሮግራም የሚከተሉትን ሰነዶች ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፦

ሀ) የተረጋገጠውን የማዕድን ክምችት መጠንና ባህርይ የሚያሳይ ማስረጃ፣

ለ) የቅድመ ምርት ወጪ ማረጋገጫ ኦዲት ሪፖርት፣

ሐ) የካፒታልና የአላቂ ዕቃዎች ዝርዝር ዕቅድና ወጪ፣

መ) የሥራ ማስኬጃ እና የማምረቻ ሥራ ዕቅድና ወጪ፣

ሠ) የአካባቢና የተፈጥሮ ሀብት ተጽእኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ እና መልሶ የማልማት ወጪ ዕቅድ፣

ረ) የመሠረተ ልማት ዕቅድና ወጪ፣

ሰ) አመልካቹ ሥራውን እንዴት እንደሚያደራጅና ክምችቱን በዘላቂነት አዋጪ በሆነ መንገድ እንደሚያመርት የሚያስረዳ ማስረጃ፣

ሸ) ሌሎች በመመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝር ሁኔታዎችን፡፡

፪/ ሥራው በተለየ መንገድ እንዲካሄድ የሚያደርግ ምክንያት ኖሮ በቅድሚያ በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ካልተፈቀደ በስተቀር የልማትና የምርት ፕሮግራሙ ከአዋጁ አንቀጽ ፴፮ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣም መሆን፣ እንዲሁም ከክምችቱ ባህርይና ሁኔታ፣ ከታቀዱ የገበያ

calendar years by presenting comprehensive environmental and social impact assessment report within 30 days before the end of the first license year.

7/ Without prejudice to the provisions of this Article, any holder of an exploration license may at any time apply and get approval to vary the work program approved in accordance with Article 21 of the Proclamation by adducing the events that prevented the licensee from carrying out the approved work program or the intended variation for more efficient work program.

## 36. Development, Production Program and Expenditures

1/ The development and production program proposed by the applicant for a small or large or as the case may be for special small scale mining license shall be accompanied with the following documents:

a) evidence showing reserve amount and characteristics of mineral deposits;

b) audit report for pre-production costs;

c) detail plan of capital and consumable goods and expenditure thereof;

d) a work plan for how to carry out production and revenue expenditure;

e) report of environment and natural resource impact assessment and expenditure plan for restoration;

f) a plan for infrastructure and expenditure thereof;

g) the way to equip and mine the deposit in sustainable and commercially significant manner;

h) other specifications to be determined by directives.

2/ The programs shall be consistent with the objectives specified in Article 36 of the Proclamation, unless a departure there from is justified and gets the prior approval of the Licensing Authority, and shall provide for the development and production of minerals in a

ሁኔታዎችና ከሌሎች ኢኮኖሚያዊና ቴክኒካዊ ሁኔታዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ማዕድኑን በዘላቂ ሁኔታ ለማልማትና ለማምረት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

፫/ የቀረበው የልማትና የምርት ፕሮግራም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተገለጹትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቀረበውን ፕሮፖዛል ያፀድቀዋል፡፡

፬/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የልማትና የምርት ፕሮግራሙ አጥጋቢ አይደለም ብሎ ሲያምን ለአስተያየቱ መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች በመግለጽ አመልካቹ ፕሮግራሙን በ፵፭ ቀናት ውስጥ አስተካክሎ እንዲያቀርብ ያስታውቀዋል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ተስተካክሎ የቀረበው ፕሮግራም የተሰጡትን አስተያየቶች በሙሉ ያላካተተ ከሆነ እና ፈቃዱ ከተሰጠ ፲ (አስር) ዓመት ያልሞላው ከሆነ ባለፈቃዱ ተጨማሪ የምርመራ ሥራ አከናውኖ የተሟላ ፕሮግራም እንዲያቀርብ የሚደረግ ሲሆን ፈቃዱ ከተሰጠ ፲ (አስር) ዓመት በላይ ከሆነው ፈቃዱ ይቋረጣል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ ፴፩ መሠረት ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የልማትና የምርት ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ ያልቻለበትን ወይም በላቀ ሁኔታ ለማከናወን የፈለገበትን ሁኔታዎች በማስረዳት የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከት ይችላል፡፡

፯/ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣንም ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የቀረበውን የስራ ፕሮግራም ለውጥ ያፀድቀዋል ወይም የማያፀድቀው ከሆነ ከነምክንያቱ በ፴ ቀናት ውስጥ ለባለፈቃዱ ያስታውቀዋል፡፡

sustainable manner consistent with the nature and characteristics of the deposit, projected market conditions and other economic and technical factors.

3/ Where the proposed development and production program meet the requirements specified under sub-article (1) and (2) of this Article the Licensing Authority shall approve the proposal.

4/ Where the Licensing Authority finds that the proposed development and production program are inadequate taking into account all relevant circumstances, it shall state the comments and notify the applicant in writing to rectify the program within 45 days.

5/ Where the rectified work program fails to meet the comments forwarded pursuant to sub-article (4) of this Article, and if the duration of the license does not exceed 10 years, the licensee shall be given another chance to rectify the program so as to meet the comments, but if the duration of the license exceeds 10 years the license shall be terminated.

6/ Without prejudice to the provisions of this Article, any holder of mining license may at any time apply and get approval to vary the approved work program in accordance with Article 31 of the Proclamation by adducing the events that prevented the licensee from carrying out the approved work program or the intended variation for more efficient work program.

7/ The Licensing Authority, when it deems appropriate, approve the proposed work program or reject the proposal of the work program and notify to the licensee within 30 days.

## ፴፯. ስለቅጥርና ሥልጠና

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፴፮(፩) ፊደል ተራ (ሸ) ስለቅጥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለፈቃድ አንድን የሥራ መደብ ለመሙላት ብቁ የሆነ ኢትዮጵያዊ ማግኘት አለመቻሉን የሚያስረዳ ማስረጃ ሲያቀርብና ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አረጋግጦ ፈቃድ ሲሰጥ ብቁ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ሊቀጥር ይችላል፡፡

፪ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የሚቀጠሩት የውጭ አገር ዜጎችና ቤተሰቦቻቸው ወደ አገር ውስጥ የመግቢያና የመኖሪያ ፈቃድ ከሚመለከተው የመንግሥት መስሪያ ቤት እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የውጪ አገር ዜጋ እንዲቀጥር የተፈቀደለት ባለፈቃድ አግባብ ያለው ክህሎትና ዕውቀት የሚተላለፍለት ተተኪ ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ አብሮ የሚሠራበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

፬/ የውጭ አገር ዜግነት ያለው ባለሙያ ዕውቀቱንና ክህሎቱን ለኢትዮጵያዊ ሠራተኛ በበቂ ሁኔታ ለማስተላለፍ የሠራበት ጊዜ በቂ መሆኑን ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በክትትል ሂደት ሲያረጋግጥ ባለፈቃዱ የውጪ አገር ዜጋውን በኢትዮጵያዊ ባለሙያ መተካት አለበት፡፡

፭/ የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታና ሥልጠና አሠጣጥ ከሥራው ባህርይና ደረጃ ጋር የተጣጣመ እንዲሁም ሥራው በተቀላጠፈና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ማካሄድ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

## ፴፰. ስለጤንነትና ደህንነት

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ ወኪሎቹ እና ሠራተኞቹ ላይ አደጋ ሊያስከትሉና በሽታ ሊያመጡ የሚችሉ ሁኔታዎችን የመለየት እና የመከላከል ሥራ መሥራት፣ ተገቢ የሆኑ የሥራ ልብሶችንና የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችን እና ሌሎች ለጤንነትና ደህንነት አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶችን ማቅረብ፣ ከዚሁ ጋር የተያያዙ ሥልጠናዎችን መስጠት፣ እንዲሁም ተገቢውን ሥልጠና ያገኙ መሆናቸውን እና ለሥራው ብቁ ሆነው መገኘታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 37. Employment and Training

1/ Without prejudice to paragraph (h) of Article 36(1) of the Proclamation, any licensee may employ a qualified foreign national, if provides evidence that shows a qualified Ethiopian national cannot be found to fill a position and obtains approval and permission thereof from the Licensing Authority.

2/ The Licensing Authority shall provide support to the licensee in order to obtain from concerned government office entry and residence permit for foreign nationals and their dependents in Ethiopia.

3/ A licensee who has obtained a permission to employ a foreign national, in accordance with sub-article (1) of this Article, shall facilitate a condition for a foreign national to work with and to transfer his skills and knowledge to an Ethiopian national.

4/ The foreign national shall be replaced by Ethiopian national where it is verified by the Licensing Authority that the foreign national has been working for enough time to transfer his skills and knowledge to an Ethiopian national.

5/ The employment condition and training provided shall commensurate with the nature and extent of operation; and the operation shall be conducted in efficient and economic manner.

## 38. Health and safety

1/ Any licensee shall identify any possible causes of occupational injury and diseases against his agents and employees undertake preventive measures, provide appropriate clothing, protective equipment and other health and safety equipment and shall ensure that they are properly trained and qualified for the work.

፪/ ባለፈቃዱ ከሥራው ባህርይና ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የጤናና የሕክምና አገልግሎት ለወኪሎቹ እና ሠራተኞቹ ማቅረብና ለሥራው የሚያስፈልጉ ፈንጂዎችና ኬሚካሎች አደጋ በማያደርሱና አግባብ ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ጥንቃቄ በተሞላበት አኳኋን እንዲጓጓዙ፣ እንዲከማቹ፣ እንዲያዙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሥርዓቶችን መከተል አለበት፡፡

፫/ ባለፈቃዱ በማንኛውም ሰው ላይ የሞት ወይም የአካል ጉዳት ከደረሰ ወይም በማናቸውም ንብረት ወይም ሥራ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ድርጊት ወይም ሁኔታ ሲከሰት ወዲያውኑ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማሳወቅና ሁኔታው የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች መውሰድ አለበት፡፡

## ፴፱.ስለአካባቢ ጥበቃ

፩/ የምርመራ ሥራ፣ የልዩ አነስተኛ፣ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በፈቃዱ እና በኪራይ በያዘው ክልል በፀደቀው የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ሪፖርት እና በአካባቢ ማኔጅመንት ዕቅዱ መሠረት የፈቃድ ዘመኑ ከመጠናቀቁ ወይም ፈቃዱ ከመቋረጡ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ ወይም ለሌላ የወደፊት ጠቀሜታ እንዲውል ለማስቻል በየደረጃው መልሶ የማቋቋም ወይም የማስተካከል እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

፪/ ባለፈቃዱ በማናቸውም በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ያልተጠበቀ ድርጊት ወይም ሁኔታ ሲከሰት ወዲያውኑ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን እና ለአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ማሳወቅና ሁኔታው የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመቀነስ ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች መውሰድ አለበት፡፡

፫/ ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ለሥራው የቆፈራቸውን ጉድጓዶች መድፈን፣ በቆረጣቸው ዛፎች ምትክ ችግኞችን መትከል እና ሌሎች አግባብ ባላቸው የአካባቢ ጥበቃ ሕጎች የተደነገጉትን የመፈጸም ግዴታ ያለበት ሲሆን እንደ ሜርኩሪ ያሉ ተመሳሳይ ጎጂ ንጥረ ነገሮችን መጠቀም አይፈቀድለትም፡፡

2/ The licensee shall provide to his agents and employees appropriate health and medical facilities commensurate with the level and nature of operations; transport, store, handle and use explosives and chemicals in accordance with appropriate laws and follow up safe and prudent procedures.

3/ The licensee shall immediately notify the Licensing Authority of any act or occurrence which has resulted in loss of life or injury to any person or which may jeopardize any property or operations and shall immediately take measures necessary to mitigate the impact of such situation.

## 39. Environmental protection

1/ The holder of an exploration, special small scale, small scale or large scale mining license prior to termination of the license shall progressively restore or reclaim the land covered by a license so that the area has to be completely restored or reclaimed for beneficial future use, in the way specified on his approved report of environmental impact assessment, and environmental management plan.

2/ The licensee shall immediately notify the Licensing Authority and the Ministry of Environment, Forest and Climate Change of any act or occurrence which may jeopardize the environment or operation, and shall immediately take measure necessary to mitigate the impact of such situation or to rehabilitate thereof.

3/ The holder of an artisanal mining license shall fill pits he dug and plant seedlings instead of trees he cut, observe other obligations stipulated under proper environmental laws and shall not be allowed to use mercury or similar materials in his operation.

፬/ የማዕድን ማምረት ሥራ ከተዘጋ በኋላ መሬቱ በዘላቂነት የሚለማበትና የሚተዳደርበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፵.ስለአካባቢ ተፅዕኖ መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፷፪(፪) መሠረት የምርመራ፣ የልዩ አነስተኛ፣ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ከአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ በጀት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ፈንድ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በቀጥታ መቆጣጠር በሚችልበት አኳኋን በየዓመቱ የመጀመሪያ ወር ውስጥ በዝግ የባንክ ሂሳብ ያስቀምጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተቀመጠው ፈንድ የማዕድን ሥራው ሲዘጋ ለማዕድን ሥራው መዘጋት አገልግሎት ላይ ውሎ የማይበቃ ሆኖ ሲገኝ ባለፈቃዱ ተጨማሪ ገንዘብ በመመደብ ሥራውን ማጠናቀቅ አለበት፡፡

፫/ ባለፈቃዱ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የማዕድን ሥራ ቦታውን ከዘጋና በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ይኸው ከተረጋገጠ ካስቀመጠው ገንዘብ የሚተርፈው ካለ እንዲለቀቅለት ይደረጋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተቀማጭ የሚሆነው ፈንድ አከፋፈል የሚሰላው ባለፈቃዱ የማዕድን ማምረት ሥራው ሲዘጋ መልሶ ለማቋቋም የመደበውን አስፈላጊ ወጪ በስምምነቱ ለተመለከተው ፈቃድ ዘመን እኩል ተካፍሎ የየዓመቱን ድርሻ በዝግ ሂሳብ በእያንዳንዱ የፈቃድ ዓመት በማስቀመጥ ይሆናል፡፡

፭/ የማዕድን ሥራው የሚዘጋበት ጊዜ ከፈቃድ ዘመኑ ያነሰ ሲሆን በየዓመቱ በዝግ ሂሳብ የሚያስቀምጠው ፈንድ ከምርት ሥራ ዕቅዱ ጋር ተጣጥሞ የተሰላ መሆን ይኖርበታል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ያስቀመጠው ገንዘብ ለባለፈቃዱ የሚለቀቀው በፀደቀው የመልሶ ማቋቋሚያ ፕሮግራም መሠረት የአካባቢ ማኔጅመንት ሥራውን ማከናወኑ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

፯/ የማዕድን ማምረት ሥራው ሲዘጋ ባለፈቃዱ መልሶ ለማቃናት እና ለመዝጋት የሚያስፈልገውን ወጪ በፀደቀው የመልሶ ማቃናት ዕቅድ መሠረት ለማከናወን እንዲችል ፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን በማስፈቀድ በየጊዜው ከዝግ ሂሳቡ በማውጣት መጠቀም ይችላል፡፡

4/ After closure of mining operation, the sustainable development and management of the land shall be specified by directives.

**40. Environmental impact Restoration fund**

1/ The holder of exploration, special small scale, small scale or large scale mining license shall, pursuant to Article 62(2) of the Proclamation, at the first month of each year deposit funds that commensurate with the environmental impact assessment on closed bank account which is subject to the direct supervision of the Licensing Authority.

2/ When the fund deposited became insufficient for closure of mining site upon termination of the mining license, the licensee shall allocate additional fund to finalize the closure.

3/ Whereas, after the licensee clears the area with the expected standard and the Licensing Authority approves same, the reserve fund found in excess, if any, shall be released for the licensee.

4/ The fund to be deposited by the licensee pursuant to sub-article (1) of this Article to carry out the restoration work during closure shall be computed by dividing the amount of fund for the agreed license period and by depositing same amount every year.

5/ If the closure of mining operation takes place earlier than the license period, the fund subject to closed bank account shall be computed in a manner that correspond with production program.

6/ The fund which is deposited for restoration works pursuant to this Article, shall be released, only when it is proved that the licensee has fulfilled his obligation on the basis of the approved restoration program.

7/ During closure of the mining operation, the licensee with the prior permission of the Licensing Authority shall utilize the fund from the closed bank account to rehabilitate the environment in accordance with the ratified environmental impact assessment plan.

**፵፩.ስለ ማህበረሰብ ልማት ተሳትፎ**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፷፪(፫) መሠረት የልዩ አነስተኛ፣ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በማህበረሰብ ልማት ዕቅድ የመሳተፍና ለዚህ የሚስፈልግ ወጪ እንደሚከተለው መመደብ አለበት፡

ሀ) በማዕድን ማምረት ቅድመ ዝግጅት ጊዜ ሲሆን በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ ለማምረት ቅድመ ዝግጅት ጊዜ ከሚመደበው ካፒታል ላይ እንደሚከተለው ይከፍላል፡

(፩) ከኮንስትራክሽን እና ለኢንዱስትሪ ማዕድናት 1%፤

(፪) ከከበሩ እና በከፊል ለከበሩ ማዕድናት 0.2%፤

(፫) ከብረት፣ ለፖታሽ እና ለብረት-ነክ ማዕድናት 0.1%፤

(፬) ከድንጋይ ከሰል 0.7%፡፡

ለ) በማዕድን ማምረት ጊዜ ሲሆን በየዓመቱ ከሥራ ማስኬጃ ወጪ ወይም ከተጣራ ትርፍ 2%፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) መሠረት የሚመደበው ፈንድ ከትርፍ ወይም ከዓመቱ ሥራ ማስኬጃ ወጪ ተሰልቶ ከሚገኘው ገንዘብ ውስጥ በመጠን የሚበልጠው ይወሰዳል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሚገኘው ፈንድ የሚከናወነው የማህበረሰብ ልማት በአካባቢው ነዋሪዎች ፍላጐት ላይ የተመሠረተ እና የአገሪቱን የልማት አቅጣጫና ደረጃ የጠበቀ መሆኑን ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሲያረጋግጥ በማህበረሰቡ እና በአካባቢው አስተዳደር ኃላፊነት የሚከናወን ይሆናል፡፡ የፈንድ አጠቃቀም ሪፖርት ለባለስልጣኑ መቅረብና ባለፈቃዱም በግልባጭ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡

፫/ የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ እንደ አግባቡ መጠኑ ከፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ጋር በሚደረገው ድርድር በሚወሰነው መሰረት ለማህበረሰብ ልማት የሚውል ፈንድ ይመድባል፡፡

፬/ የማህበረሰብ ልማት ፕሮግራሙ የሚያቅፋቸው የፈቃድ ክልሉ አካባቢ ነዋሪዎች፣ የቦታ ክልል አወሳሰን እና የልማት ፈንድ አስተዳደር ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**41. Participation in Community Development**

1/ Pursuant to Article 62(3) of the Proclamation, the holder of special small, small and large scale mining license or as appropriate, exploration license, shall participate in Community Development Plan and allocate money for such expenses as follows:

a) during mining development preparation period, lump sum amount from operation cost of the development period shall be paid as follows:

(1) construction or industry minerals 1%;

(2) precious or semi-precious minerals 0.2%;

(3) iron or potash or metallic minerals 0.1%;

(4) coal 0.7% .

b) during mining period, from annual revenue expenditure or net profit 2%;

c) the fund allocated pursuant to paragraph (b) of this sub-article shall be which ever higher from the annual revenue expenditure and the net profit.

2/ The community development activity carried out by the fund acquired pursuant to sub-article (1) of this Article, shall be implement when the Licensing Authority approves that it is in line with the countries development strategy and to the expected standard; and under the supervision of the community and the respective administrative organ. The report on the appropriation of the fund shall be submitted to the Licensing Authority copied to the licensee as well.

3/ The holder of exploration license shall, as the case may be, allocate community development fund on the basis of negotiation with Licensing Authority.

4/ The boundary of the local community, who are living around the license area and the area to be encompassed under the community development plan and fund administration, shall be determined by the directive of the Ministry.

**፵፪.ስለ መዛግብት፣ ሪከርድ እና ሪፖርት**

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ የሚከተሉትን የያዘና በእነዚህ ላይ የሚደረጉ ወቅታዊ ለውጦችን የሚያሳይ መዝገብ በኢትዮጵያ ውስጥ መያዝ አለበት፦

ሀ) የተከናወኑ የማዕድን ሥራዎችን፣ የተገኙ ውጤቶች እና ወጪዎችን፣

ለ) በየሥራ መደባቸው በመለየት የጠቅላላ ሠራተኞችን የሥራ ሁኔታዎች እና የተከሰቱ አደጋዎችን፣

ሐ) የተመረቱትን፣ የተከማቹትን፣ የተዘጋጁትን፣ የተጓጓዙትን፣ ወደ ውጭ ይተላኩትንና የተሸጡትን ማዕድናት ዝርዝር፣ ጥራት እና ዋጋ፣

መ) የዕቃዎች፣ መሣሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችንና ሌሎች ንብረቶች ዝርዝር፡፡

፪/ ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ከፈቃድ ሥፍራው የተወሰዱ የኮር ናሙናዎችን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊነት ያላቸው የማዕድን ናሙናዎችን ቅጂ እና ከፈቃዱ ጋር የተያያዙ የቴክኒክ፣ የላብራቶሪ እና የሌሎች ሪፖርቶችን ቅጂዎችን በጥንቃቄ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

፫/ የቅኝት ባለፍቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱትን የያዘ የዓመቱን አጠቃላይ ሪፖርት የፈቃዱ ዓመት ከማለቁ በፊት ባሉት የመጨረሻዎች ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

፬/ የምርመራ ባለፈቃድ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የዓመቱን አጠቃላይ ሪፖርት የፈቃድ ዓመቱ ከማለቁ በፊት ባሉት የመጨረሻዎቹ ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፦

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (መ) የተዘረዘሩ መረጃዎችን፣

ለ) በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም የተመለከቱትን እንደአግባቡ በየደረጃው የተከናወኑ የሪሞት ሴንሲንግ፣የጂኦሎጂ፣ የጂኦፊዚክስ፣የጂኦኬሚስትሪ፣ የቁፋሮ ሥራዎችን ጨምሮ ሌሎች የተከናወኑ የማዕድን ሥራዎችን፣ የተገኙ ውጤቶችን፣ የተሠሩ ካርታዎችን፣ ያልተተነተኑ ኦርጂናል ዳታዎች የወረቀት እና ዲጂታል ቅጂ እና ሌሎች ተመሳሳይ መረጃዎችን፣

**42. Books , Records and Reports**

1/ Any licensee shall maintain records in Ethiopia during the term of the license and current changes with regards to these records as follows:

a) operations, its outputs and expenditures;

b) all employees by category of their labor, conditions of their job and accidents happened;

c) inventories of all minerals produced, stored, treated, transported, exported and sold, along with its quality and prices;

d) inventories of all equipments, machineries, vehicles and other assets.

2/ Any licensee during the term of the license shall carefully maintain duplicate of core samples of minerals taken from the license area and copies of all other relevant mineral samples, technical, laboratory and other reports relating to the license.

3/ The holder of reconnaissance license shall submit to the licensing authority a published general annual report which includes the details specified under paragraph (a) and (b) of sub-article (1) of this Article within 30 days prior to the end of each license year.

4/ The holder of an exploration license shall submit to the Licensing Authority the general annual report which includes the following within 30 days prior to the end of license year:

a) the information's specified under paragraph (a), (b) and (d) of sub-article (1) of this Article;

b) on the basis of the approved work program, as the case may be, remote sensing undertaken at different levels, geology, geophysics, geochemistry works, excavations, and other mining works and the result thereof, maps, hard and soft copies of raw data and other similar information;

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፊደል ተራ (ለ) የተመለከቱትን ሥራዎች ለማከናወን በሥራ ላይ የዋለ የወጪ ዝርዝር በየወጪ መደቡ የተያዙ መረጃዎችን፣

መ) በየሥራ ምድቡ የተሰማሩትን ሠራተኞች፣ ሥራዎች የተካሄዱባቸው ጠቅላላ የሥራ ቀናት ብዛት እንዲሁም የሥራ ሁኔታዎችን እና አደጋዎች፣

ሠ) ለማዕድን ሥራው ቀረጥ ተከፍሎባቸው ወይም ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነፃ ሆነው የገቡ እና በሥራ ላይ የዋሉ ዕቃዎች፣ መሣሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችንና የሌሎች ንብረቶችን ዝርዝር እና በእነዚህ ላይ የተደረጉ ለውጦችን፣

ረ) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ያስፈልጋል ብሎ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መረጃዎች፡፡

፭/ ይዞ የመቆየት ፈቃድ ባለይዞታ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፬)፣ (፭) እና (፮) መሠረት ፈቃዱ መጀመሪያ ሲሰጥ በቀረቡ መረጃዎች ላይ የተደረጉ ለውጦችን፣ እንዲሁም የቀጠሉ ሁኔታዎችንና ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ያስፈልጋል ብሎ በመመሪያ የሚወስናቸውን ሌሎች መረጃዎች ያካተተ ዓመታዊ ሪፖርት እያንዳንዱ የፈቃድ ዓመት ካለቀ በኋላ ባሉት የመጀመሪያዎቹ ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

፮/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፍቃድ እያንዳንዱ ሩብ ዓመት ካለቀ በኋላ ባሉት የመጀመሪያዎቹ ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን አጠቃሎ የያዘ የሩብ ዓመት ሪፖርት ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፊደል ተራ (ሐ) እና (መ) የተመለከቱ መረጃዎችን፣

ለ) በየደረጃው የተሰሩ የጂኦሎጂ ስራዎችንና የተገኙ ውጤቶችን ጨምሮ የተከናወኑ የማዕድን ሥራዎችን በአጠቃላይ እንዲሁም የማዕድን ምርት ሁኔታ እና በቀሪው ክምችት ላይ ያለውን ለውጥ፣

c) detail expenditure incurred to undertake works specified under paragraph (b) of sub article (4) of this Article, and information maintained at each category of expenditure;

d) the number of employees deployed to each category of works, the total number of working days, work conditions and accidents;

e) inventory of all equipments, machineries, vehicles or other materials physical asset employed for the mining works and which are imported with or without custom duties and taxes and any change there in;

f) other information determined by the directives of the Licensing Authority, as may be necessary.

5/ The holder of retention license shall submit annual report to the Licensing Authority, within 30 days after the expiry of each year, which specify change made to the original information submitted during application for license pursuant to Article 5 (4) ,(5) and (6) of this Regulation and the information still continued to prevail after the mining operation and other information determined as important by the Licensing Authority.

6/ The holder of a small scale or a large scale mining license shall submit summary reports to the Licensing Authority on a quarterly basis, within thirty days after the end of each period which contains the following:

a) the information specified under paragraph (c) and (d) of sub-article (4) of this Article;

b) all operations, including the geological works and the progress and results thereof, and the conditions relating to production of minerals and any change in the reserve of the deposit;

ሐ) የተመረቱትን፣ የተከማቹትን፣ የተዘጋጁትን፣ የተጓጓዙትን፣ የተሸጡትን፣ ወደ ውጪ የተላኩትን ወይም ሌላ ዋጋ ጪምሮ የማዕድናት ዝርዝር እና የማዕድኑን መድረሻ ሥፍራ፣ የገገርዎችን ዜግነት፣ እንዲሁም ከጠቅላላው ሽያጭ የተገኘውን ገቢ፣ የሮያልቲ መጠን ከነስሌቱ፣

c) an inventory of all minerals produced, stored, treated, transported, sold and exported and destination and nationality of buyers for all exports, revenue collected from sales, the amount of royalty and its computation;

መ) በአካባቢ ማኔጅመንት ዕቅድ መሠረት የተከናወኑ የማህበረሰብ ልማት እና መልሶ የማቋቋም ሥራዎች ዝርዝር እና ወጪ፣

d) on the basis of environmental management plan, works carried out for community development and restoration and expenses thereof;

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተመለከቱትን ሥራዎች ለማከናወን በሥራ ላይ የዋለ የወጪ ዝርዝር በየወጪ መደቡ፣

e) detail of expenditure incurred, in respect to its category, to carry out works specified under this sub-article;

ረ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያስፈልጋሉ ብሎ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መረጃዎች፡፡

f) Such other information as the licensing authority may determines by the directives.

፯/ የልዩ አነስተኛ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፍቃድ እያንዳንዱ የፈቃድ ዓመት ካለቀ በኋላ ባሉት የመጨረሻዎቹ ፷ ቀናት ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፮ ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ እና (ረ) የተዘረዘሩትን መረጃዎች፣ እንዲሁም የገቢ ግብር መጠን ከነስሌቱ የያዘ አጠቃላይ ዓመታዊ ሪፖርት እና በውጪ ኦዲተር የተረጋገጠ ወቅታዊ የኦዲት ሪፖርት ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

7/ The holder of a special small scale mining licensee shall submit to the Licensing Authority within 60 days after the end of each year; information specified under paragraph (a), (c), (d), (e) and (f) of sub-article (6) of this Article, annual general report with income tax and current audit report approved by external auditor.

፰/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፍቃድ እያንዳንዱ ሩብ አመት እና የፈቃድ ዓመት ካለቀ በኋላ ባሉት የመጨረሻዎቹ ፷ ቀናት ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፮ የተዘረዘሩትን መረጃዎች፣ የገቢ ግብር እና የመንግስት ነፃ የአክሲዮን ድርሻ መጠን ከነስሌቱ የያዘ አጠቃላይ ዓመታዊ ሪፖርት እና በውጪ ኦዲተር የተረጋገጠ ወቅታዊ የኦዲት ሪፖርት ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

8/ The holder of a, small or large scale mining license shall submit; information specified under sub-article (6) of this Article, annual general report with income tax and government participation interest, current audit report approved by external auditor to the Licensing Authority within 60 days after the end of each quarter and each year.

## ፵፫.ፈቃድን ስለማሳየት

አግባብ ያለው የመንግሥት ባለሥልጣን፣ ሕጋዊ ባለይዞታ የሆነ ሰው ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ሌላ ሰው በፈቃድ ክልል በመገኘት ፈቃዱን ለማየት ሲጠይቅ ማንኛውም ባለፈቃድ ዋናውን ፈቃድ ወይም በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ትክክለኛነቱ የተረጋገጠውን የፈቃዱን ኮፒ ማቅረብና ማሳየት አለበት፡፡

## 43. Presentation of License.

Any licensee shall produce the license or a copy thereof certified by the Licensing Authority whenever so requested by an appropriate public officer, law full occupant of the license area or other interested person by being in the license area.

## ክፍል አምስት

## ስለ ሮያልቲ፣ የገቢ ግብር፣የመንግስት ነፃ አክሲዮን ድርሻ፣ ስለፈቃድ ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎች

### ፵፬.ስለ ሮያልቲ፣ የገቢ ግብር እና የመንግስት ነፃ አክሲዮን ድርሻ ክፍያ

፩/ ማንኛውም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ ፷፭(፪) መሠረት የሚከፍለው ሮያልቲ የሚሰላው ማዕድኑ በተመረተበት ሥፍራ በሚኖረው ዋጋ ላይ ተመስርቶ ሲሆን ክፍያው የሚፈጸመው እያንዳንዱ ሩብ ዓመት ከተፈጸመ በኋላ ባሉት በመጀመሪያዎቹ ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

፪/ ማንኛውም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በስምምነት ሰነዱ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ ፷፯ እና በገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት በየዓመቱ ለሚመለከተው የግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት የትርፍ ግብር በመክፈል ማስረጃውን ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፸፪ ድንጋጌ መሠረት የከፍተኛ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ከኢንቨስትመንቱ ፭% (አምስት በመቶ) የሚሆነውን ነፃ የመንግሥት የአክሲዮን ድርሻ ግብር ከተከፈለበት ትርፍ ላይ በማስላት በየዓመቱ ለሚመለከተው የመንግስት ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ገቢ ማድረግና የከፈለበትን ደረሰኝ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡ ትርፉ ለባለድርሻዎች ያልተከፋፈለም ከሆነ የመንግስት ነጻ አክሲዮን ድርሻ ፭% ተሰልቶ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

፬/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እንደ አስፈላጊነቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት የተፈጸሙትን ክፍያዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አግባብ ያላቸውን የባለፈቃዱን ሰነዶች ይመረምራል፡፡

### ፵፭.የሮያልቲ ክፍያን ስለመቀነስ፤ ለጊዜው ስለማንሳት ወይም ስለማስቀረት

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ ማንኛውም ማዕድን ማምረት የጀመረ ባለፈቃድ ሊከፍል የሚገባውን የሮያልቲ ክፍያ ለመቀነስ፣ ለጊዜው ለማንሳት

## PART FIVE

## ROYALTY, INCOME TAX, FREE GOVERNMENT PARTICIPATION INTEREST AND OTHER PAYMENTS

### 44. Royalty, Mining Income Tax and Free Government Participation Interest.

1/ The royalty payable by holder of large scale mining license, pursuant to Article 65 (2) of the Proclamation, shall be computed and levied ad valorem, at the production site and shall be paid on quarterly basis within 30 days after the end of the period to which it relates.

2/ Any holder of large scale mining license shall, as specified in the agreement, within the time to declare profit and loss statements in his balance sheets, make payment annually for the concerned revenue collecting authority, as stipulated under Article 67 of the Proclamation and provisions of Income Tax Proclamation and shall submit the receipt thereof to the Licensing Authority.

3/ Any holder of large scale mining license, from the net income pursuant to Article 72 of the Proclamation shall pay 5% (five percent) of Government equity annually to the revenue collecting authority and submit the receipt of payment to the Licensing Authority. Where the profit is not distributed among beneficiaries, 5% free equity of the Government shall be paid.

4/ The Licensing Authority, as the case may be, shall examine the necessary documents of the licensee in order to confirm the correctness of the payment effected pursuant to sub-article (2) and (3) of this Article.

### 45. Reduction, Temporary lifting or Waiver of the liability to pay Royalty

After verifying the existence of the following reasons, the Licensing Authority may recommend to the Council of Minister or the concerned Regional Authority reduction,

ወይም ለማስቀረት እንዲቻል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም እንደአግባቡ ለሚመለከተው የክልል የመንግስት አካል ሀሳብ ሊያቀርብ ይችላል:

፩/ የማዕድን ፈቃድ ሲሰጥ ከነበረው የገበያ ሁኔታ አንፃር ያልታሰበ እና ዓለም አቀፋዊ የሆነ የጎላ የዋጋ ቅናሽ ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ሲያጋጥም፣

፪/ ስትራቴጂካዊ ነው ብሎ መንግስት የወሰነው ማዕድን መመረቱ ብቻ በቂ ሆኖ ሲገኝ፣

፫/ እንደ ብረት ያሉ ማዕድናትን የጎላ ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚሰጥ መልኩ እሴት በመጨመር ሲያመርት፡፡

## ፵፮.<u>ስለፈቃድ ክፍያዎች</u>

፩/ ማንኛውም የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚጠይቅ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ ፸፩ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ መሠረት ለእያንዳንዱ ብሎክ የሚከፍለው የፈቃድ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፣

ሀ) ለቅኝት ሥራ ፈቃድ ብር ፫ሺ፱፻፬ (ሶስት ሺ ዘጠኝ መቶ አራት ብር)፣

ለ) ለምርመራ ሥራ ፈቃድ ብር ፬ሺ፰፻፴፯ (አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ሰባት ብር)፣

ሐ) ለይዞ መቆየት ፈቃድ ብር ፱ሺ፰፻፩ (ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ አንድ ብር)፣

መ) ለአነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ወይም የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃድ ብር ፬ሺ፪፻፯ (አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰባት ብር)፣

ሠ) ለከፍተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ወይም የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃድ ብር ፭ሺ፩፻፴፪ (አምስት ሺህ አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ብር)፣

ረ) ለአነስተኛ ደረጃ የከበሩ፣ በከፊል የከበሩ፣ ለብረት ነክ እና ለሌሎች ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃዶች ብር ፯ሺ፭፻፳ (ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሀያ ብር)፣

ሰ) ለከፍተኛ ደረጃ ለከበሩ፣ በከፊል ለከበሩ፣ ለብረት ነክ እና ለሌሎች ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃዶች ብር ፰ሺ፫፻፷ (ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ ብር)፣

temporary lifting or waiver of the liability to pay royalty of a licensee who commence mining:

1/ where there are international adverse market conditions unforeseen during the issuance of a license and results sharp price reduction for not less than a year;

2/ any mineral which Government designates as strategic minerals and the production thereof by itself found to be adequate;

3/ when licensee produces metallic minerals like iron by adding value in a way it significantly contribute for national economy.

## 46.<u>License Fees</u>

1/ The license fees to be paid by any applicant, for each specific block of a license, pursuant to Article 71 of the Proclamation and Article 14 of this Regulation, shall be as follows:

a) Reconnaissance license .......Birr 3,904

b) Exploration license .............Birr 4,837

c) Retention license.............. ...Birr 9 ,801

d) small scale industrial and construction mining license ...................Birr 4,207

e) large scale industrial and construction mining license.....................Birr 5,132

f) precious, semi-precious, metallic and other minirals of small scale mining license ..............................Birr 7,520

g) precious, semi-precious, metallic and other minirals of large scale mining license ..............................Birr 8360

፪/ ማንኛውም የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለማሳደስ የሚጠይቅ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ ፸፩ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ ለእያንዳንዱ ብሎክ የሚከፍለው የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፡

ሀ) ለምርመራ ሥራ ፈቃድ ብር ፫ሺ፶፰ (ሶስት ሺህ ሀምሳ ስምንት ብር)፤

ለ) ለይዞ መቆየት ፈቃድ ብር ፲ሺ፩፻፺፩ (አስር ሺህ አንድ መቶ ዘጠና አንድ ብር)፤

ሐ) ለአነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ወይም የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃድ ብር ፪ሺ፰፻፷፱ (ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ብር)፤

መ) ለከፍተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ወይም የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃድ ብር ፬ሺ፸፰ (አራት ሺህ ሰባ ስምንት ብር)፤

ሠ) ለአነስተኛ ደረጃ ለከበሩ፣ በከፊል ለከበሩ፣ ለብረት ነክ እና ለሌሎች ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃዶች ብር ፮ሺ፩፻፲፯ (ስድስት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር)፤

ረ) ለከበሩ፣ በከፊል ለከበሩ፣ ለብረት ነክ እና ለሌሎች ማዕድናት ለከፍተኛ ደረጃ ማምረት ሥራ ፈቃዶች ብር ፰ሺ፬፻፲፩ (ስምንት ሺህ አራት መቶ አስራ አንድ ብር)::

፫/ ከከፍተኛ ደረጃ ኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ፈቃድ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ ፶፬(፩) መሠረት ለሚሰጡ ፈቃዶች መከፈል የሚገባቸው ክፍያዎችን በሚመለከት በክልል ሕጎች ይወሰናል፡፡

## ፵፯.ሌሎች ክፍያዎች

፩/ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት አመልካቾች በዚህ አንቀጽ የተመለከቱ አገልግሎት ክፍያዎችን መፈጸም አለባቸው፡፡

፪/ ማመልከቻ ወይም ሰነድ ለማስመዝገብ የሚከተሉት ክፍያዎች መፈጸም አለባቸው፡

ሀ) የማዕድን ሥራ ፈቃዶችን ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ምዝገባ ብር ፬፻፩ (አራት መቶ አንድ ብር)፤

ለ) የፈቃድ መብትን ለማስተላለፍ ለሚቀርብ ማመልከቻ ምዝገባ ብር ፰፻፷፬ (ስምንት መቶ ስልሳ አራት ብር)፤

2/ The renewal fee to be paid by any license holder for each block of a license, pursuant to Article 71 of the Proclamation and Article 14 of this Regulation, shall be as follows:

a) Exploration license........... Birr 3,058

b) Retention license .............Birr 10,191

c) Small scale industrial and construction mining license ....................Birr 2,869

d) Large scale industrial and construction mining license ..................Birr 4078

e) Precious, semi-precious, metallic and others minerals of small scale mining license .................................Birr 6117

f) Precious, semi-precious, metallic and others minerals of large scale mining license ...........................Birr 8411

3/ Except the mining license of large scale construction minerals, the amount of license fees to be paid for licenses granted as per Article 54 (1) of the Proclamation shall be determined by the laws of the Regional States.

## 47. Other payments

1/ Applicant shall pay service fees provide under the provisions of this Article to obtain different services provided by the Licensing Authority.

2/ For registration of application or documents the following fees shall be paid:

a) registration of application for mining works license.....................Birr 401

b) registration of application for transfer of license rights .......................Birr 864

ሐ) የማማከር አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለሚቀርብ ማመልከቻ ምዝገባ ብር ፩፻(አንድ መቶ ብር)፣

መ) የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለሚቀርብ ማመልከቻ ምዝገባ ብር ፩ሺ(አንድ ሺህ ብር)፣

ሠ) የግኝት ሰርተፊኬት ለማግኘት ለሚቀርብ ማመልከቻ ምዝገባ ብር ፲ (አስር ብር)፣

ረ) ሰነድ ለማስመዝገብ ብር ፶ (ሀምሳ ብር)፡፡

፫/ የተለያዩ ሰነዶችን ለመውሰድ የሚከተሉት ክፍያዎች መፈፀም አለባቸው፡

ሀ) የፈቃድ ሰነድ በገጽ ብር ፳ (ሀያ ብር)፣

ለ) የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ብር ፬፻ (አራት መቶ ብር)፣

ሐ) ለቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ብር ፪ሺ፮፻፶፱ (ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሀምሳ ዘጠኝ ብር)፣

መ) ለግኝት የምስክር ወረቀት በገጽ ብር ፪፻ (ሁለት መቶ ብር)፣

ሠ) የጠፋ፣ የተቃጠለ፣ የተበላሸ ወይም የተሰረቀ የፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት ምትክ በገጽ ብር ፴ (ሰላሳ ብር)፣

ረ) የዋናው ፈቃድ ወይም ምስክር ወረቀት ተጨማሪ ቅጅ ብር ፫፻ (ሶስት መቶ ብር)፣

ሰ) የማማከር ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተጨማሪ ቅጂ ብር ፫፻ (ሶስት መቶ ብር)፣

ሸ) የቴክኒክ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተጨማሪ ቅጂ ብር ፬፻፷ (አራት መቶ ስልሳ)፣

ቀ) የታደሰ ፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት ብር ፪፻ (ሁለት መቶ ብር)፡፡

፬/ የማዕድን ናሙናዎችን ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ ለሚቀርብ ጥያቄ የአገልግሎት ክፍያ መጠን የማዕድናቱን ዓይነትና ክብደት መሠረት በማድረግ ሚኒስቴሩ በጥናት ላይ ተመስርቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ያስወስናል፡፡

፭/ ከማዕድን ሥራዎች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን የሚያሳይ ካርታ ለማግኘት እና በዚህ አንቀጽ ያልተዘረዘሩ ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚፈጸሙ ክፍያዎችን ሚኒስቴሩ በጥናት ላይ ተመስርቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ያስወስናል፡፡

c) registration of application to get certificate of professional competence for consultancy service……………Birr 100

d) registration of application to get certificate of competence for technical service……………………..Birr 1000

e) registration of application to get certificate of discovery……….. Birr 10

f) registration of document…………Birr 50

3/ For receiving different documents the following fees shall be paid:

a) license document per/page……..Birr 20

b) certificate of professional competence for consultancy service … .Birr 400

c) certificate of competency for technical service ……………………..Birr 2659

d) certificate of discovery per/page ………………………………Birr 200

e) substitute of lost, burned, damaged or stolen license or certificate per/page ……………………………...Birr 30

f) additional copy of original license or certificate……………………..Birr 300

g) additional copy of a certificate of professional competence for consultancy service ………………………..Birr 300

h) additional copy of a certificate of competency for technical service ………………………………...Birr 460

i) a renewed license or certificate…Birr 200

4/ A service fee for application to export sample minerals shall be determined by the Council of Ministers Regulations based on the study of the Ministry by taking into account the weight and type of the mineral.

5/ A service fee to obtain copies of maps pertaining to mining operations and such other services not specified under this Article shall be determined by the Council of Ministers Regulations based on the study of the Ministry.

፮/ ከከፍተኛ ደረጃ ኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ፈቃድ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ ፶፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለሚሰጡ ፈቃዶች እና ሌሎች አገልግሎቶች የሚፈጸሙ የአገልግሎት ክፍያዎች በየክልሎቹ ሕጎች ይወሰናል፡፡

## ፵፰.<u>ክፍያን አለመፈጸም ወይም ማዘግየት</u>

በአዋጁ አንቀጽ ፷፯ እንዲሁም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፮ መሠረት መፈጸም ያለበት ማንኛውም ክፍያ በወቅቱ ካልተፈጸመ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ክፍያው በመዘግየቱ ወይም ባለመፈጸሙ ምክንያት በዚህ ደንብ ክፍል ስድስት ድንጋጌዎች መሠረት ሊወሰድ የሚችለው የቅጣት እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ገንዘቡ ላልተከፈለበት ወይም ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም ከወር ላነሰ ጊዜ ፪ በመቶ መቀጫ ተጨምሮበት እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ጥፋቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶች</u>

## ፵፱.<u>አንደኛ ደረጃ ጥፋቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶች</u>

፩/ ማንኛውም ሰው፡

ሀ) የአዋጁ አንቀጽ ፯ (፫) እና (፭) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በቅድሚያ ተገቢውን ፈቃድ ሳይዝ በማዕድን ሥራ ላይ ከተሠማራ እና ማዕድናትን ሲያዘዋውር ከተገኘ፣

ለ) ከፈቃድ ማመልከቻ፣ ከግኝት ማስታወቂያ ወይም ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጥያቄ እና ዕድሳት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሀሰተኛ መረጃ ከሰጠ ወይም ካጭበረበረ፣

ከብር ፫፻ሺ. (ሶስት መቶ ሺህ ብር) እስከ ፭፻ሺ. (አምስት መቶ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ ያለፈቃድ ያመረተው ማዕድንም ይወረሳል፡፡

፪/ ማንኛውም ባለፈቃድ፡

ሀ) የማዕድን ሥራዎችን በግዴለሽነት ወይም ሆን ብሎ አግባብ ባልሆነ መንገድ ካካሄደ ወይም የፈቃዱን መሠረታዊ ስምምነቶች ወይም ግዴታዎች ከጣሰ፣

6/ Except the mining license of large scale construction minerals, fees for licenses and other services provided pursuant to Article 54 (1) of the Proclamation shall be determined by the laws of the respective Regional State.

## 48. <u>Failure to Pay or Late Payment</u>

Without prejudice to any other recourses that the Licensing Authority take pursuant to the provisions of Part Six of this Regulation, failure to pay or delay of payments specified under Article 67 of the Proclamation and Article 46 of this Regulation shall subject to a fine of 2% for each month or part thereof for the amount remains unpaid.

## <u>PART SIX</u>

## <u>OFFENCES AND ADMINISTRATIVE PENALTIES</u>

## 49. <u>First Level Offences and Administrative penalties</u>

1/ Any person who:

a) without prejudice to the provisions of Article 7(3) and (5) of the Proclamation, undertakes mining operations and transport minerals without having obtained the relevant license;

b) has submitted false or fraudulent information in connection with the application relating to a license, renewal, notification of discovery, or certificate of competence;

shall be punishable with a fine from Birr 300,000 up to Birr 500,000 and the mineral produced without having license shall be confiscated.

2/ Any licensee who:

a) conducts mining operation in a reckless or willfully improper manner or breaches any material term or conditions of his license;

ለ) በአዋጁ አንቀጽ ፷፱ መሠረት የተሰጠውን ትእዛዝ ካልፈጸመና መክፈል ያለበትን ክፍያ ካልፈጸመ፣

ሐ) ከፈቃድ መብቱ በተያያዘ ማናቸውንም የማጭበርበር ድርጊት ከፈጸመ፣ ወይም ከማዕድን ሥራው ጋር በተያያዘ ሀሰተኛ መረጃ ከሰጠ፣ በፈቃድ ስምምነቱ ከተመለከተው ውጪ ሌላ የማዕድን ሥራ ሲያከናውን ከተገኘ፣

መ) የተፈጥሮ አካባቢን፣ ጤንነትንና ደህንነትን፣ ወይም ሌሎች የማዕድን ሥራዎችን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ከጣሰ፤ወይም

ሠ) በተጨባጭ ሁኔታ የማዕድን ሥራዎችን የሚመለከቱ አስተዳደራዊና የፋይናንስ ግዴታዎችን ካልተወጣ፣

የማዕድን ፈቃዱ ተሰርዞ ከብር ፻፶ሺ. (አንድ መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) እስከ ፪፻ሺ. (ሁለት መቶ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፶.ሁለተኛ ደረጃ ጥፋቶች እና ቅጣቶች

ማንኛውም ባለፈቃድ፡

፩/ እንደአግባቡ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፪ (፩) ድንጋጌ የተመለከቱትን መዝገቦችና ሪከርዶችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን ወይም ማቴሪያሎችን ካልያዘ ወይም መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም ያልተሟሉ መዝገቦችና ሪከርዶችን ከያዘ፣

፪/ የማዕድን ሥራዎችን በቸልተኝነት ወይም የማንኛውንም ሰው ጤንነት ወይም ደህንነት፣ አካባቢንና ተፈጥሮን በሚጎዳ መልኩ ካከናወነ ወይም ስለ ማህበረሰብ ልማት የሚጠበቅበትን ግዴታ ካልተወጣ ወይም የማዕድን ክምችቱን አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ ካካሄደ፣ በአጠቃላይ ተገቢ የማዕድን አሰራር ልምዶችን ካልተከተለ ወይም ፈቃዱ የሚያስከትልበትን ግዴታ ካልተወጣ፣

፫/ ሥልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቆጣጣሪ ወይም ሠራተኛ በፈቃድ ወደ ተያዘው ክልል እንዳይገባ ወይም የማዕድን ሥራዎች የሚካሄዱባቸውን ቦታዎች ወይም ተቋሞች ወይም የባለፈቃዱን መዝገቦች፣ ሪከርዶች ወይም ሌሎች ሰነዶች ወይም ማቴሪያሎች እንዳያይ ካደረገ ወይም በሠራተኛው የተሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ካልፈጸመ፣



b) fails to comply with an order and the financial obligations prescribed under Article 69 of the Proclamation;

c) commits any kind of fraudulent act in relation to rights emanated from a license or has submitted false information or commits fraudulent act in connection with mining operations or undertakes mining activities not envisaged in the license;

d) breach the environmental, safety and health standards or fails to observe an obligations related to his mining operation; or

e) fails materially to meet administrative and fiscal obligations related to his mining operation;

shall be punishable with a fine from Birr 150,000 up to Birr 200,000.

## 50.Second Level Offences and penalties

Any licensee who:

1/ fails to maintain, as the case may be, books and records required under sub-article of Article 42 (1) of this Regulation or other documents or materials required or maintains books and records which are materially incorrect or incomplete;

2/ conducts mining operations in a negligent manner or in a way which endangers the health or safety of any person, the environment and nature, a deposit, or fails to observe his duties in respect to community development or fails to observe generally accepted good mining practices or fails to observe an obligation of license;

3/ fails to grant a duly authorized supervisor or official of the Licensing Authority access into the license area, or to any other site or premises of the mining operations or to his books, records, other documents or materials, or fails to carry out a lawful order or instruction of such official;

፬/ የማማከር እና የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት የማዕድን ኢንዱስትሪው የሚጠይቀውን ወቅታዊ የሙያ ብቃትና ቴክኖሎጂ ያገናዘበ እንዲሁም ሙያዊ ሥነ ምግባርን ያሟላ አገልግሎት መስጠት ካልቻለ፣

የፈጸመውን የጥፋት ድርጊት ለማረም ወዲያውኑ እርምጃ ከወሰደ ከብር ፶ሺ (ሀምሳ ሺህ ብር) እስከ ፸ሺ (ሰባ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ ጥፋቱን ለማረም ወዲያውኑ የእርምት እርምጃ ካልወሰደ የገንዘብ ቅጣቱ እጥፍ ይሆናል፤ ጥፋቱ በማንኛውም ሰው ጤንነት ወይም ደህንነት በተፈጥሮ አካባቢ ወይም በማዕድን ላይ ሊደርስ የተቃረበ ወይም ቀጣይነት ያለው ጉዳት ካስከተለ፣ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ባለፈቃዱ ጥፋቱን እስከሚያስተካክል ድረስ የማዕድን ሥራዎቹን ወዲያውኑ እንዲያቆም ያደርጋል፤ የጥፋቱ ድርጊት ወይም ሁኔታ እስኪስተካከል ፈቃዱ ታግዶ ይቆያል።

## ፶፩.ሦስተኛ ደረጃ ጥፋቶች እና ቅጣቶች

ማንኛውም ባለፈቃድ፣

፩/ መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ትክክለኛ ያልሆኑ ወይም ያልተሟሉ መዝገቦችንና ሪከርዶችን የመያዝ ጉድለቶችን ሳይጨምር፣ የተሟሉ ትክክለኛ የሆኑና ወቅታዊውን ሁኔታ የሚያሣዩ መዝገቦችንና ሪከርዶችን ካልያዘ፣

፪/ ተፈላጊ ሪፖርቶችንና ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረበ ወይም ተፈላጊ መግለጫዎችን በወቅቱ ካልሰጠ፣

፫/ ጥፋቱ የማንኛውም ሰው ጤንነት ወይም ደህንነት፣ የተፈጥሮ አካባቢን ወይም የማዕድኑን ክምችት አደጋ ላይ የማይጥል ቢሆንም የማዕድን ሥራዎቹን ተገቢ በሆነ መንገድና በጥንቃቄ ካልፈፀመ ወይም ደንቦችንና መመሪያዎችን ካላከበረ፣

፬/ ከማዕድን ሥራ ፈቃድ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በሀገሪቱ የሥራ ቋንቋ ወይም በእንግሊዝኛ ካልያዘ፣

ማስጠንቀቂያ እንደደረሰው ወዲያውኑ የእርምት እርምጃ ካልወሰደ ወይም የጥፋት ድርጊቱ ሊታረም የማይችል ከሆነ ከብር ፴ሺ (ሰላሳ ሺህ ብር) እስከ ፶ሺ (ሀምሳ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

4/ where the holder of a certificate of competence for consultancy and technical service failed to carry out his duties in an ethical manner, to use modern technology and generally accepted good mining operation practices in the mining industry;

shall be punishable with a fine Birr 50,000 up to Birr 70,000, if immediately takes remedial action to correct the violation after receiving notice; if the person concerned does not take remedial action immediately, the amount of the fine shall be doubled; if the violation results in an imminent or continuing danger to the health and safety of any person, the environment or a deposit, the Licensing Authority may immediately order suspension of mining operations license pending the correction of the violation, and the license shall be suspended until such act, omission or condition is rectified.

## 51.Third Level Offences and penalties

Any licensee who:

1/ fails to maintain books and records in a complete, accurate and current manner, excluding such deficiencies to maintain books and records which are materially incorrect or incomplete;

b) fails in a timely manner to file all reports and other documents or to give notices required; .

c) fails to carry out mining operations in a proper and prudent manner or to observe regulations or directives but which failure does not endanger the health or safety of any person, the environment or a deposit;

d) fails to maintain information in connection with mining license either in Amharic or English language;

shall be punishable with a fine from Birr 30,000 up to Birr 50,000 if fails to take remedial measure to correct the violation immediately after receiving notice.

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፶፪.ጊዜን ስለማሳጠር ወይም ስለማራዘም እና ስለ ምርት ፕሮግራም ማሻሻል

፩/ የዚህ ደንብ የተለያዩ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በበቂ ምክንያት የባለፈቃዱን መብት በማይነካ ሁኔታ ወይም በፈቃዱ ወይም በአዋጁ የተመለከቱ ተግባሮቹንና ግዴታዎቹን በመፈጸም አቅሙ ላይ ተጽእኖ በማያመጣ ሁኔታ በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከቱት ተግባራት መፈጸም የሚገባቸው ጊዜ እንዲያጥር ወይም እንዲራዘም ሊወስን ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለፈቃድ በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ሥራውን ማከናወን ያልቻለ መሆኑን በማስረዳት የፈቃድ ጊዜው እንዲራዘምለት ሊጠይቅ ይችላል፤ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣንም የቀረበው ምክንያት በቂ መሆኑን ሲያምንበት የፈቃድ ጊዜው እንዲራዘም ሊፈቅድለት ይችላል፤ ሆኖም የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄውን ያልተቀበለው ከሆነ ይህንኑ ውሳኔ ከነምክንያቱ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዓለም ላይ በሚከሰቱ የገበያ፣ የኢኮኖሚና የቴክኖሎጂ ሁኔታዎች የተነሳ የሚያበረታታ ለውጥ መኖሩን በተጨባጭ ማስረጃ ያረጋገጠ እንደሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ መሠረት ቀርቦ የፀደቀውን የልማትና የምርት ፕሮግራም ባለፈቃዱ እንዲያሻሽል ሊያደርገው ይችላል፤ ሆኖም ለውጡ በፈቃዱ ወይም በአዋጁ የተመለከቱትን ተግባሮችና ግዴታዎቹን በመፈጸም ዕቅድ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆን የለበትም፡፡

### ፶፫.የማዕድን ማምረት ሥራ የሚጀምርበትን ጊዜ ስለማስረዘም ወይም ስለማሳጠር

የአዋጁ አንቀጽ ፴ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ የሚጀመርበትን የሁለት ዓመት ጊዜ በሚከተለው መስፈርት መሰረት በስምምነት ወቅት ሊያሳጥረው ወይም ሊያስረዝመው ይችላል፡

## PART SEVEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 52. Shortening or Extension of time and Variation of Production Program

1/ Notwithstanding some provisions of this Regulation, the Licensing Authority may, for good cause without jeopardizing the rights of a licensee or negatively affecting his ability to perform the duties and obligations specified under the license or the Proclamation, shorten or extend periods specified within this Regulation to execute certain activities.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, any licensee by demonstrating the events that prevent him from carrying out the approved work program, may apply for an extension of a license period; where the Licensing Authority satisfied with the adequacy of the reason provided, may grant extension of license period; if it rejects the request for an extension it shall notify same in writing within 30 days by stating the reason for refusal.

3/ The Licensing Authority if ascertains with concrete evidence the improvement of global situation with regard to market conditions, economic factors and technology, it may require the licensee to improve the development and production program approved pursuant to Article 11 of this Regulation; provided, however, that such variation shall not jeopardize a licensee to perform his duties and obligations specified under the license or the Proclamation.

### 53. Extending or Shortening the Period to Commence Mining

Without prejudice to the provision of Article 30 of the Proclamation, the Licensing Authority may extend or shorten the two years period to commence the small or large scale mining based on the following criteria:

፩/ ለማስረዘም፡

ሀ) ማዕድኑ ከጽንስ በመሬት ውስጥ ለውስጥ በመቆፈር ዘዴ የሚመረት ሲሆን፣

ለ) ማዕድኑ በተፈጥሮ ባለው አስቸጋሪ አቀማመጥ የተነሳ በቀላሉ ለአመራረት የማይመች ሲሆን፣ ወይም

ሐ) የማዕድኑ አመራረት የተለያዩ የአሰራር ደረጃዎችን ማለፍ ያለበትና የተለየ የአመራረት ስልት የሚጠይቅ ሲሆን፡፡

፪/ ለማሳጠር፡

ሀ) የፅንስ ማዕድን በቀላል ጉድጓድ ቁፋሮ ዘዴ የሚመረት ሲሆን፣

ለ) ማዕድኑ ከደለል የሚመረት ሲሆን፣

ሐ) ማዕድኑ ያለው የተፈጥሮ አቀማመጥ ለአመራረት አመቺ ሲሆን፣ ወይም

መ) ማዕድኑን ለማምረት የተለያየ የአሰራር ደረጃዎች ውስጥ የማያልፍ ሲሆን፡፡

## ፶፬ ለባለፈቃዶች ስለሚሰጥ የመንግሥት ድጋፍ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፸፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገነው መሠረት ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በባህላዊ የአመራረት ዘዴ ለሚከናወኑ የከበሩና በከፊል የከበሩ የማዕድን ማምረት ሥራዎች በሚከተለው አኳኋን ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፣

ሀ) የማዕድን ክምችት ያለበትን ሥፍራ ለይቶ በመከለል የባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች ብቻ እንዲሰማሩበት የማድረግ፣

ለ) የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍና ሥልጠና የመስጠት፣

ሐ) ለሥራቸው የሚሆን የገንዘብ ድጋፍና የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ የመርዳት፣

መ) በፈቃደኝነት የሚመሠረቱ የማዕድን አምራቾች የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲቋቋሙና ሥራቸውን እንዲያካሂዱ የመርዳት፣

ሠ) የተመረቱ ማዕድናትን በማዘጋጀት፣በማጓጓዝew፣ በማከማቸትና ለገበያ በማቅረብ ረገድ ምክር የመስጠት፣

1/ extension of period where:

a) the mining is carried out by digging from the primary deposit by under-ground mining method;

b) it is difficult to mine, because of the complex nature of the mineral; or

c) the mineral requires special procedure and passes through different methods to mine.

2/ shortening of period where:

a) the primary mineral is extracted by simple open-pit method;

b) the mining is from placer minerals;

c) the nature of the mineral is simple for mining; or

d) the method of mining of the mineral do not pass through different procedure.

## 54. Government Assistance

1/ Pursuant to Article 77(1) of the Proclamation, the Licensing Authority may, where it deems appropriate, provide assistance for small and micro enterprises engaged in precious and semi-precious minerals operation by holding an artisanal mining license in the following manner:

a) identify and delimit mineral deposits for mining operations only to be undertaken by artisanal miners;

b) provide technical and administrative assistance and training;

c) assist in obtaining financial support and loan for such operations;

d) assist in the voluntary formation and the functioning of small and micro enterprises producers;

e) advise on the treatment, transportation, storage and marketing of minerals produced by such licensees;

ረ) የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው በባህላዊ የአመራረት ዘዴ ሲያመርቱ ለነበሩና ወደ ልዩ አነስተኛ የማዕድን ማምረት ደረጃ ለመሸጋገር በቂ ዝግጅት ላላቸው ድጋፍ የመስጠት፣

ሰ) የጌጣጌጥ ማዕድናት ላይ እሴት ጨምረው ለገበያ የማቅረብ ሥራ ለሚሰሩ ባለፈቃዶች ድጋፍ እንዲያገኙ የማድረግ፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እንደ አስፈላጊነቱ ከሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ፍላጎቶች አንጻር ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በመፈተሽ ለማዕድን ምርመራ እና አነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የተሻለ የፋይናንስና የቴክኖሎጂ ምንጮች እንዲያገኙ በዘርፉ ከሚገኙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር የሥራ ግንኙነት፣ የልምድ ልውውጥ፣ የተለያዩ ሥልጠናዎችና ሌሎችም ድጋፎችን በሁለትዮሽ ስምምነት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

## ፶፭.የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ሚኒስቴሩን የሚያማክር የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ምክር ቤቱ፦

ሀ) ከሚኒስቴሩ፣ ከክልል የማዕድን ቢሮ ወይም ከኤጀንሲ፣

ለ) ከፌደራል ወይም ከሚመለከታቸው የክልል የአካበቢና የደን ጥበቃ አካላት፣

ሐ)ከንግድ ሚኒስቴር፣

መ) ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣

ሠ) ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣

ረ) ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣

ሰ) በማዕድን ዘርፍ የጎላ ሚና ካላቸው የአገር ውስጥ ባለሀብቶች፣

ሸ) መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣

f) provide assistance to those who have been engaged in operation of precious and semi-precious minerals by holding an artisanal morning license, if the licensee are adequately prepared to transform to the stage of special small scale mining;

g) provide assistance for the licensees engaged in adding value on precious minerals and supply them for market.

2/ The Licensing Authority shall, as appropriate, by assessing the socio-economic interest of the country, facilitate conditions necessary for creation of work relationship, experience sharing, training and other supports for an exploration and small scale mining license holders to obtain finance, acquire an improved technology through bilateral agreements with governmental and non-governmental organization.

## 55.Mining Operations Advisory Council

1/ Pursuant to sub-article (2) of Article 55 of the Proclamation, to advise the Ministry, the Mining Operations Advisory Council (hereinafter the "Council") is hereby established.

2/ The Council shall have Chairperson and members drawn from the following organs by the Minister and be assigned by the Government:

a) Ministry, regional mining bureau or agency;

b) the concerned environmental protection organs of federal government or regional states;

c) Ministry of Trade,

d) Ministry of Finance and Economic Cooperation;

e) Ministry of Industry,

f) Ethiopian Revenue and Custom Authority;

g) domestic investor playing significant role in the mining sector;

h) non-governmental organizations;

ቀ) ከማዕድን ሥራዎች ጋር ተዛማጅነት ካላቸው የሙያ ማህበራት፣ እና

በ) እንደ አስፈላጊነቱ ከሌሎች አግባብ ካላቸው አካላት

የተውጣጡ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሰየም ሰብሳቢና አባላት ይኖሩታል፡፡

፫/ የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት፡

ሀ) የአገሪቱን የማዕድን ዘርፍ ከወቅቱ ዓለም አቀፍ የማዕድን ኢንዱስትሪው ጋር ተወዳዳሪ በማድረግ በዘርፉ የግል ባለሃብቶችን ተሳትፎ ለማሳደግና ዘላቂ የሆነ አገራዊ ጥቅምን ለማረጋገጥ የሚያስችል የፖሊሲና የሕግ ማሻሻያ ሀሳቦችን ለሚኒስትሩ የማቅረብና የማማከር፣

ለ) የማዕድን ሥራዎች በሚከናወኑበት አካባቢ ከማዕድን ሥራው ጋር በተያያዘ ከአካባቢው ማህበረሰብ እና በየደረጃው ከሚገኙ የአስፈጻሚ አካላት ጋር የሚነሱ አለመግባባቶች ሲኖሩ ችግሮቹ የሚፈቱበትን መንገድ ለሚኒስቴሩ የማማከር

ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

፬/ የምክር ቤቱ ስብሰባ፡

ሀ) ምክር ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሲሆን ሰብሳቢው በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

ለ) ከግማሽ በላይ የምክር ቤት አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

ሐ) የምክር ቤቱ ምክረ-ሀሳቦች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ ለሁለት እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

መ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥርዓትና አሠራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፭/ የምክር ቤት አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም አንድ አባል እንደገና በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት ሲሰየም ለሁለተኛ የሥራ ዘመን ሊያገለግል ይችላል፡፡

i) professional associations related with mining operations; and

j) members from other appropriate organs when ever necessary.

3/ The Council shall have the powers and responsibilities to:

a) provide advise to the Ministry on amendment of policies and laws on how to make the countries' mining sector competitive in respect of the contemporary international mining industries standards, thereby increasing the role of investors in the mining sector by creating an enabling environment and ensuring the national interest of the country in sustainable manner;

b) render advise to the Ministry on how to settle disputes arising around the mining areas with the local community and administrative organ at each level in relation to mining operations.

4/ Meeting of the Council:

a) the Council shall have a regular meeting twice a year, provided, however, the Chairperson may at any time call an extra-ordinary meeting whenever necessary;

b) there shall be quorum where more than half of the members are present at a meeting;

c) recommendations of the Council shall be passed by a majority vote; in case of ties, the Chairperson shall have casting vote;

d) without prejudice to the provisions of this sub-article the Council may adopt its own meeting rules of procedures.

5/ The term of members of the Council shall be five years; provided, however, a member may serve for second terms if recommended by the Minister and re-assigned by the Government.

፮/ መንግሥት በማናቸውም ምክንያት አንድን ምክር ቤት አባል ከምክር ቤት አባልነቱ ማንሣትና መተካት ይችላል፡ አባላት በፈቃዳቸው ወይም በሌላ ምክንያት ሊለቁም ይችላሉ፡፡

፯/ የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

## ፶፮.የተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማዕድን ሥራዎችን ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ እንቅስቃሴዎች የሚቆጣጠር ተቆጣጣሪ ይመድባል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመደበ ተቆጣጣሪዎች ለቁጥጥር ተግባር ሲሄዱ ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያ እና ቁጥጥር ለማድረግ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተሰጠ የተቆጣጣሪነት ልዩ መታወቂያ ማሳየት አለባቸው፡፡

፫/ ተቆጣጣሪዎች ለቁጥጥር ተግባር መንቀሳቀስ የሚችሉት በመንግስት የሥራ ሰዓት ይሆናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ከመንግስት የሥራ ሰዓት ውጪ ለቁጥጥር ሥራ የሚሄዱ ከሆነ አግባብ ካለው ባለስልጣን ይህንኑ የሚያስረዳ ደብዳቤ መያዝ አለባቸው፡፡

፭/ የፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች በተለይ በሚሰጥ ውክልና አዋጁንና የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ቁጥጥር ማካሄድ ይችላሉ፡፡

## ፶፯.የተሻሩ ሕጎች

የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፹፪/፲፱፻፹፮ ተሽሮ በዚህ ደንብ ተተክቷል፡፡

## ፶፰.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

6/ Government may remove member of the Council at any time on any ground and substitute or member of the Council may resign voluntarily or for any reason.

7/ The Council shall be accountable to the Prime Minister.

## 56. Powers and Duties of the Inspectors

1/ The Licensing Authority shall assign inspectors to inspect the technical and administrative aspects of mining operations.

2/ The inspectors assigned pursuant to sub-article (1) of this Article shall show their identification cards and special identification cards pertaining to their inspection duties issued by the Licensing Authority as they inspect operation.

3/ Inspectors shall inspect business establishments at government official working hours.

4/ Notwithstanding sub-article (2) of this Article, inspectors conduct inspection during out of official working hours shall possess a letter issued by the Licensing Authority for such purpose.

5/ The other officials of the Licensing Authority may carry out necessary inspection activities when special delegation is given to them by the Licensing Authority.

## 57. Repealed Laws

The Council of Ministers Mining Operations Regulation No. 182/1994 is hereby repealed and replaced by this Regulation.

## 58.Effective Date

This Regulation shall enter in to force on the date of its publication in the *Federal Negarit Gazeta*

**Done at Addis Ababa this 24th Day of January, 2018.**

**HAILEMARIAM DESALEGN**

**PRIME MINISTER OF FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**